# የኢትዮጵያን የመወለድ ሕግ በሚመለከት የተደረገ ተጨማሪ ጥናት

ለልዩ ልዩ ሕጐች አጥኚ ዓለም አቀፍ አካዳሚ ዘጠነኛ ጠቅላላ ጉባኤ በጆርጅ ክሪችናቪች* የቀረበ

## የልዩ ልዩ አገር ሕጎች አጥኚ ዓለም አቀፍ አካዳሚ

ለዘጠነኛው ዓለም አቀፍ አካዳሚ ጠቅላላ ጉባኤ የቀረበውን ጽሑፍ ከመመልከታችን በፊት ፣ የአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የሕግ ፋኩልቲ ከአካዳሚው ጋር ስለ አደረጋቸው ግንኙነቶች አጭር መግቢያ መስጠቱ ተገቢ ይመስለኛል ።

የአካዳሚው ጠቅላላ ጉባኤዎች በአራት ዓመት አንድ ጊዜ ይደረጋሉ ። የዚህ ጽሑፍ አቅራቢ ፤

እ ኤ አ በ፲፱፻፷፪ ዓ/ም ሐምቡርግ ላይ ተደርጎ በነበረው በስድስተኛው ጠቅላላ ጉባኤ ላይ ፣ የኢትዮጵያን ፓርላማ የተግባር ክልሎች (ይህ ጽሑፍ በኢትዮጵያ ጥናቶች መጽሔት ፫ኛ ቮልዩም ገጽ ፷፫ ላይ በ፲፱፻፷፫ ዓ/ም እ ኤ አ ወጥቷል) ፤

እ ኤ አ ፲፱፻፷፮ ዓ/ም ኡፕሳላ ላይ ተደርጎ በነበረው በሰባተኛው ጠቅላላ ጉባኤ ላይ ፣ በኢትዮጵያ ከጋብቻ ውጭ መወለድን የሚደነግጉ ሕጎችን (ይህ ጽሑፍ በኢትዮጵያ የሕግ መጽሔት ፫ኛ ቮልዩም ገጽ ፩፻፲፩ ላይ በ፲፱፻፷፯ እ ኤ አ ቀርቧል) ፤

እ ኤ አ በ፲፱፻፸ ዓ/ም ፒስካራ ላይ ተደርጎ በነበረው በስምንተኛው ጠቅላላ ጉባኤ ላይ ፣ በኢትዮጵያ ፍትሐ ብሔር ሕግ ርትዕ ስላለው ሚና (ይህ ጽሑፍ በአፍሪቃ የሕግ መጽሔት ፫ኛ ቮልዩም ገጽ ፩፻፵፮ ላይ በ፲፱፻፷፱ ዓ/ም እ ኤ አ ወጥቷል) የሚያወሱ ሪፖርቶችን በማቅረብ የሕግ ፋኩልቲውን ወክዬ ተሳትፌአለሁ ።

እንዲሁም አካዳሚው እ ኤ አ በ፲፱፻፸፬ ዓ/ም ቴህራን ላይ ባደረገው በዘጠነኛው ጠቅላላ ጉባኤ ላይ ፋኩልቲው በዶ/ር ፋሲል ናሆም አማካይነት ሦስት ጽሑፎችን በማቅረብ የተሳተፈ ሲሆን ፣ በመጨረሻም እ ኤ አ በ፲፱፻፸፰ ዓ/ም ቡዳፔስት ላይ ተደርጎ በነበረው በአሥረኛው ጠቅላላ ጉባኤ እኔ ተገኝቼ አንድ በእኔ የተጻፈና ሌላ አቶ የኔካአል የኋላ እሸት በተባሉ የሕግ ባለሙያ የተዘጋጀ ጽሑፍ በማቅረብ ተሳትፌአለሁ ።

ሪፖርቶች ሁሉ በአካዳሚው መዝገብ ቤት ውስጥ በሚገባ የተቀመጡ ሲሆን ፣ ዝርዝራቸውም በአካዳሚው እትሞች ውስጥ ተጠቅሶአል ።

አካዳሚው የሚያወጣቸውን እትሞች መከታተልና ከአካዳሚው ጋር ግንኙነት ማድረግ ፣ ሕጎቻቸው ከተለያዩ የሕግ ሥርዓቶች ተቀናጅተው ለተነደፉና በአንድ በተወሰነ የሕግ ሥርዓት (ለምሳሌ በእንግሊዝ ወይም በፈረንሳይ) አቅጣጫ የተቀየሰ የሕግ ሥርዓት ለሌላቸው የአፍሪቃ አገሮች የተለየ ጠቃሚነት አለው ። የኢትዮጵያ የሕግ ሥርዓት ከተለያዩ የሕግ ሥርዓቶች መመንጨቱ ጎልቶ የሚታይና በማደግም ላይ ያለ መሆኑ ፣ ከነዚህ አገሮች መካከል ኢትዮጵያን አንዷና ዋነኛዋ ያደርጋታል ። አካዳሚው በጉባኤዎቹና በሪፖርቶቹ አማካይነት የሚያደርጋቸው ጥናቶች እና ምርምሮች ይህን በአገር የማይወሰነውን የሕግ ሳይንስ እድገት ያፋጥኑታል ።

ባለፉት ሁለት ጉባኤዎች ካቀረብሁዋቸው ጽሑፎች አንደኛው በዚህ እትም የሚወጣ ሲሆን ሌላው ደግሞ በሚቀጥለው እትም ይወጣል ። ሁለቱም ሪፖርቶች ወቅታዊ ርዕሶችን የሚመለከቱ ናቸው ። በቅርቡ ያሻሻልሁት አንደኛው ጽሑፍ በፍርድ ቤቶች አካባቢም ሆነ ከፍርድ ቤቶች ውጭ አከራካሪ የሆነውን መወለድን የሚመለከት ነው ። ይህ ጽሑፍ አዲስ አቅጣጫዎችን በሚጠቁም እ ኤ አ በ፲፱፻፸፱ ዓ/ም በተዘጋጀው ማከያና ከተወሰነ ዘግየት ባለ አስተያየት የተሰጠበት ፍርድ የተደገፈ ነው ። እ ኤ አ በ፲፱፻፸፰ ዓ/ም የቀረበው ሁለተኛው ጽሑፍ ደግሞ ከኤኮኖሚ እድገት ጋር አብሮ የሚመጣውንና አዲስ የሕግ ችግሮች የሚያስነሳውን በተመረቱ ዕቃዎች መነሻ የሚመጣ ኃላፊነትን የሚመለከት ነው ።

* የሕግ ፕሮፌሰር ፣ ሕግ ፋኩልቲ ፣ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ

# መ ግ ቢ ያ

አሁን የማቀርበው ሪፖርት መሠረተ ሐሳብ ከዚህ ቀደም በሰባተኛው ጠቅላላ ጉባኤ "ከጋብቻ ውጭ መወለድን የሚደነግጉ ሕጎችን" በሚመለከት ከተወያየንበት ርእስ ጋር ይደራረባል ። በሰባተኛው ጠቅላላ ጉባኤ የተገኘሁት እኔው በርእሱ[1] ላይ በወቅቱ ሰፋ ያለ ሪፖርት ያቀረብሁ ስለሆነ ፣ መደጋገም እንዳይሆን[2] በማለት በዚህ ጽሑፍ ርእሱን ከተለየ አቅጣጫ እመለከተዋለሁ ።

ሌላው ችግር የርዕሱን ስያሜ የሚመለከት ነው ። በኢትዮጵያ ሕግ በሰፊው የሚሠራበት "አባትነትና እናትነት የሚታወቅበት መንገድ" (ሕጋዊ ግምት) በጋብቻም ሆነ ከጋብቻ ውጭ መወለድን ለማስረዳት ያገለግላል ። የመወለድን ማስረጃ የሚመለከተው ክፍል ድንጋጌዎችም ቢሆኑ ፣ ለሁሉም ልጆች በተመሳሳይነት የሚያገለግሉ ናቸው ።[3] የመወለድ ውጤቶችም እንደ ዚሁ በማንኛውም ሁኔታዎች ተመሳሳይ ናቸው ። ስለ ሆነም ልጆችን በመከፋፈል በሰባተኛው ጠቅላላ ጉባኤ "የተፍጥሮ ልጆች" መባሉ ወይም በዘጠነኛው ጠቅላላ ጉባኤ "ከጋብቻ ውጭ የተወለዱ ልጆች" መባሉ ፣ ለኢትዮጵያ ሕግ ምንም ልዩነት አያስከትልም ። በዚህ ምክንያት በዋና ሪፖርተሩ[4] የተነደፈውን የሪፖርቱን አቀራረብ ስልትና የሪፖርቱን ርእስ ለመለወጥ ተገድጃለሁ ።

በመሠረቱ ልጅነት ስለሚያስከትላቸው ውጤቶች ከመነጋገሩ በፊት የማን ልጅ መሆን ስለሚረጋገጥባቸው ሁኔታዎች መነጋገሩን ማስቀደም ያስፈልጋል ። እንደ ዚሁም የእናትነት መረጋገጥ በዚሁ ላይ የሚመሠረተውን የአባትነትን መረጋገጥ ይቀድማል ። የዚህ ጽሁፍ አቀራረብም በዚህ መሠረት የተዘጋጀ ነው ። "መወለድ" የሚለውን ቃል የምንጠቀመው በልጅና በእናቱ ወይም በአባቱ መካከል ያለውን ግንኙነት ወይም መተሳሰር ለማመልከት ሲሆን ፣ "አባትነትና እናትነት" የሚታወቅበት መንገድ የሚለውን ደግሞ የመወለድን ግንኙነቶች (መተሳሰሮች) የሚፈጥሩትን ወይም የሚ መሠርቱትን ሁኔታ/ዎች ለማመልከት ነው ።

## ሀ/ እናትነት

በዚህ ርእስ የተመለከተውን ጉዳይ (፩) አመሠራረቱን (፪) የማያከራክር ማስረጃን (፫) አከራካሪ ማስረጃንና (፬) ክርክርን በተከታታይ እንመለከታለን ።

### ፩/ አመሠራረት

"በመወለድ ብቻ እናትነትን ለማስረዳት ይቻላል" (አንቀጽ ፯፻፵፱)[5]። በእናትና በልጅ መካከል ያለው ግንኙነት አንድ የአገባችም ሆነ ያላገባች ሴት ልጅ በመውለዷ ብቻ ይመሠረታል ። እዚህ ላይ ወሳኙ ጉዳይ ልጁ ከስዋ መወለዱ ብቻ ነው ።

የእናትዬዋ ስምምነት ወይም እናትነቷን መቀበል በኢትዮጵያ ሕግ አስፈላጊ አይደለም ፡(በአንዳንድ አገሮች ሕጎች ከጋብቻ ውጭ የተወለደን ልጅ በሚመለከት እናትነትን በሙሉ ለማስረዳት የእናትዮዋ ስምምነት ወይም እናትነቷን መቀበል አስፈላጊ ነው[6]) ።

### ፪/ የማያከራክር[7] የልጅነት ማስረጃ

አስተማማኝ የሆነ የልደት ማረጋገጫ መኖር ለግልም ሆነ ለአስተዳደር ሥራ ጠቃሚ ነው ። በዚህም ምክንያት የፍትሐ ብሔር ሕጋችን እናትነት እና አባትነት በሕግ እንደታዘዘው ስለመወለድ ማስታወቂያ ሲሰጥ (አንቀጽ ፩፻፩-፪) "በቅድሚያ በተዘጋጀ[8]" ለዚሁ ተግባር በተሾመ ሹም (አንቀጽ ፵፰ እና ተከታዮቹ) አማካይነት በሕዝብ ክብር መዝገብ (አንቀጽ ፲፬ እና ተከታዮቹ) በተመዘገበ የልደት ምስክር ወረቀት[9] (አንቀጽ ፯፻፶፱) መረጋገጥ እንዳለበት ይደነግጋል ፡ ይሁን እንጂ እነዚህና ሌሎች የሕዝብ ክብር መዝገብን የሚመለከቱ የሕግ አንቀጾች ፣ ልደት[10] መረጋገጥ ያለበት (በቅድሚያ ያልተዘጋጁ) "የታወቁ ጽሑፎችን" (አንቀጽ ፫ሺ፫፻፶፭-፪) በማቅረብ መሆኑን በሚገልጸው የመሸጋገሪያ አንቀጽ (አንቀጽ ፫ሺ፫፻፶፭-፩) ላልተወሰነ ጊዜ ታግደዋል[11] ። ይሁን እንጂ እነዚህን የመሰሉ የታወቁ ጽሑፎችን በማዘጋጀት ተግባር የሰለጠኑ ባለሙያዎች ስለሌሉ[12] ፤ ይህም አንቀጽ በሥራ ሊተረጐም አይችልም ። በዚህ ተግባር የሰለጠኑ ባለሙያዎች ቢኖሩም ኖሮ እንኳን ፣ ቋሚ የሆነውና ያልታገደው የሕግ አን

---

• ለዘጠነኛው ጉባኤ ቀርቦ የነበረው ይህ ሪፖርት እዚህ መጽሔት ላይ የቀረበው በመጠኑ ተሻሽሎና አዲስ ሁኔታዎችን የሚመለከት ማከያ ተጨምሮበት ነው ።

1 ይህ ሪፖርት "የቀድሞው ሪፖርት" ተብሎ በዚህ ጽሑፍ ውስጥ የሚጠቀስ ሲሆን ይዘቱም ከጉባኤው ወዲህ ከተጨመረበት ማከያ ጋር እ.ኤ.አ. በ፲፱፻፷፰ ዓ/ም በኢትዮጵያ የሕግ መጽሔት ፲፫ኛ ቮልዩም ከገጽ 511-523 ድረስ ታትሞ ወጥቷል ። እንዲሁም በዚህ ሪፖርት ላይ የተጨመረበት ማከያ በዚህ ጽሑፍ ማጠቃለያ ላይ ተጨምሮአል ።

2 በዚህ ርዕስ ላይ አዲስ ሕግ አልወጣም ።

3 በመድፈር ሥራ ወይም በመጥለፍ የሚፈጠሩ ሁኔታዎችን አይጨምርም (ከታች ይመልከቱ) ።

4 ፕሮፌሰር ጋብርኤል ካንቴር ከ ቨላዴሊድ ዩኒቨርስቲ ።

5 እንዳይደለ ካልተገለጸ በስተቀር "አንቀጽ" ሲባል የኢትዮጵያ የፍትሐ ብሔር ሕግ አንቀጽ ማለት ነው ።

6 እ.ኤ.አ. በ፲፱፻፷፯ ዓ/ም ለሰባተኛው ጠቅላላ ጉባኤ በአውሬሊያን ጆንሲኮ የቀረበውን አጠቃላይ ሪፖርት ገጽ ፰ የግርጌ ማስታወሻ ቁጥር ፪ ይመልከቱ ።

7 "የማያከራክር" ሲባል "አከራካሪ ከሆኑት ውጭ" ያሉትን ለማለት ነው ። "ስለሚያከራክሩ" የግርጌ ማስታወሻ ቁጥር 17 እና የቀድሞውን ሪፖርት ገጽ 519 ይመልከቱ ።

8 የማስረጃው አስፈላጊነት ከመፈጠሩ በፊት የተዘጋጀ ።

9 "አክት ደ ኔሳንስ" ።

10 የጋብቻና የሞትም እንደዚሁ ።

11 በነጋሪት ጋዜጣ ትእዛዝ ታትሞ እስካልወጣ ድረስ በሥራ ላይ ሊውሉ አይችሉም ።

12 ሌሎችን ሰዎች በለመሸም ለአገር አስተዳደር ሚኒስቴር የተሰጠው አማራጭ (አንቀጽ ፫ሺ፫፻፷፭-፪) ሥራ ላይ የዋለ አይመስልም ። ከጣሊያን ወረራ የተነሳ ባለሙያዎች ኤርትራ ውስጥ በመጠኑ ያሉ ይመስላል ። እ.ኤ.አ. በ፲፱፻፸፩ ዓ/ም "የማዘጋጃ ቤቶች አዋጅ" መሠረት ስለሚደረጉት የመወለድ ምዝገባዎች ሕጋዊ ተቀባይነት የቀድሞውን ሪፖርት የግርጌ ማስታወሻ ቁጥር ፳፪ ይመልከቱ ።

ቀጽ (አንቀጽ ፯፻፹) ፣ የልደት የምስክር ወረቀት በሌለበት ጊዜ መወለድ መረጋገጥ ያለበት የታወቁ ጽሑፎችን በማቅረብ ሳይሆን “የልጅነት ሁኔታ” መኖሩን በማሳየት ነው ስለሚልና ይህም አንቀጽ ከመሸጋገሪያው አንቀጽ[13] ቅድሚያ ያለው ስለሆነ ፣ የታወቁ ጽሑፎችን በማቅረብም ቢሆን መወለድን ማረጋገጥ አይቻልም ማለት ነው ። ይህ አመለካከት ከፍርድ ቤቶች አሠራር ጋር ይመሳሰላል ።

በብዙ የውጭ አገሮች ሕጎች እናትነት የሚረጋገጠው በቅድሚያ የተዘጋጀውን የልጁን የልደት የምስክር ወረቀት በማቅረብ ነው ፣ ይሁን እንጂ ከላይ በተጠቀሙት ምክንያቶች የተነሳ በኢትዮጵያ ብቸኛና ትክክለኛ የሆነው የማያከራክር የእናትነት (የአባትነትም እንደዚሁ ፣ ከታች ይመልከቱ) ማረጋገጫ ዘዴ ፣ የልጅነት ሁኔታ መኖር ይመስላል ። ልጁ በወላጁ ፣ በወላጁ ዘመዶችና በሕብረተሰቡ እንደወላጁ ልጅ ተደርጎ መያዙን ማሳየት (በአራት ምስክሮች) ያስፈልጋል (አንቀጽ ፯፻፸-፬) ። እናትነትን በሚመለከት ረገድ ይህ የማያከራክር የልጅነት ማስረጃ በሚገባ ይሠራል ።

“በሁኔታ መኖር” እናትነት የሚረጋገጠው በመሠረቱ በቃልና በተዘዋዋሪ መንገድ[14] ቢሆንም ፤ ይህንን “የሁኔታ መኖር” መቃወም የሚቻለው የሕጋዊ ሁኔታዎችን[15] አለመሟላት የሚያስረዱ አራት ምስክሮች አቅርቦ በማስመስከር ብቻ ነው (አንቀጽ ፯፻፸፭-፪) ። እናትነትን በሚመለከት ተቃውሞ የቀረበበት አንድም የከፍተኛ ፍርድ ቤት ጉዳይ[16] አላጋጠመኝም ።

### ፫/ አከራካሪ[17] ማስረጃ

እንደላይኛው ሁሉ በዚህም ረገድ እናትነትን በመቃወም[18] የቀረቡ ክርክሮች ያላጋጠሙኝ ቢሆንም ፣ ከአንቀጽ ፯፻፸፮-፯፻፹፫[19] ድረስ የተመለከቱትን ተቃውሞ ለማቅረብ አስፈላጊ የሆኑትን ሕጋዊ ሁኔታዎች መጥቀሱ ተገቢ ነው ።

የእናትነትን ሁኔታ መኖር “ለመጠየቅ” ክስ ሊቀርብ የሚችለው ጠያቂው የሁኔታው መኖር የሌለውእንደሆነ ወይም በዚሁ ሁኔታ መኖር ላይ ሕጋዊ ክርክር የተነሳበት እንደሆነ ብቻ ነው (ከላይ ይመልከቱ)[20] ከዚህም በላይ ጥያቄውን ተቀባይ የሚያደርጉ ሁኔታዎች መኖራቸውን አይቶ ፍርድ ቤት በቅድሚያ ፈቃድ ካልሰጠ በስተቀር ፤ ክሱ ሊመሠረት አይችልም ። እነዚህ ሁለት ሁኔታዎች ከተሟሉ ፣ “ልደቱን” እና “ማንነቱን” (በተወለደው ልጅና በጠያቂው መካከል) የሚያስረዱት ወይም የሚያመለክቱት ተጨባጭ ሁኔታዎች ፍርድ ቤቱን ሊያሳምኑ በሚችሉ በማናቸውም ዘዴዎች ሊረጋገጡ ይችላሉ ።[21]

### ፬/ ክርክር

በአንቀጽ ፯፻፸፱ መሠረት በቅድሚያ የፍርድ ቤት ፈቃድ ከተሰጠ (የሁኔታ መኖር ሳይኖር በአከራካሪ ማስረጃ ጊዜ እንደሚሰጠው ዓይነት)[22] ፣ አለ ተብሎ በሚታመን የእናትነት ሁኔታ ላይ በማንም ጉዳዩ በሚያገባው ሰው (አንቀጽ ፯፻፸፰) ክርክር ሊቀርብ ይችላል ። ፈቃዱ ከተገኘ በኋላ ፣ ተከራካሪው[23] የሁኔታው መኖር ባለው ሰው[24] ላይ ይህን ሁኔታ ሊፈጥሩ የሚችሉት ተጨባጭ ሁኔታዎች (ልደት ፣ ማንነት) ያለመኖራቸውን በማናቸውም ዘዴዎች ሊያረጋግጥ ይችላል ።

በእናትነት ሁኔታ መኖር ላይ (ማለትም ተከሳሽ ሁኔታውን ለማግኘት ስለሚኖረው “መብት”) በከፍተኛው ፍርድ ቤት የቀረበ ክርክር አላጋጠመኝም ። በአጠቃላይ አነጋገር ፣ እናትነት በክርክር ደረጃ የሚያስከትላቸው ችግሮች ቢኖሩ በጣም ጥቂቶች ናቸው ።

## ለ/ አባትነት

በኢትዮጵያ ውስጥ በተለያዩ ምክንያቶች[25] እናትነትን ከማረጋገጥ ይልቅ አባትነትን ማረጋገጥ የበለጠ ያስቸግራል ። ይኸንኑ የሚደነግገው ሕግ ግልጽ አይደለም ፤ ይኸን በሚመለከት ረገድ ከፍተኛ ፍርድ ቤት የሚቀርቡ ጉዳዮች ብዙ ከመሆናቸውም በላይ የተሰጡት ፍርዶችም አብዛኛውን ጊዜ አከራካሪና በሕግ አተረጓጐማቸው የተለያዩ ናቸው ። ከዚህም በላይ ራሱ ግልጽ ያልሆነው የውርስ ሕግ ጉዳይ አብሮ ይነሳል ።

---

13 ያልተስተካከለው አጻጻፍ ከችኮላ የተነሳ የመጣ ይመስላል ። ስለዚሁ “ስለኢትዮጵያ የቤተሰብ ሕግ አንዳንድ ጥያቄዎች” የኢትዮጵያ የሕግ መጽሔት ቮልዩም ፱ ገጽ 205 እና የቤተሰብ ሕግ ጥያቄዎች ቁጥር 245 (ሕግ ፋኩልቲ ፤ አዲስ አበባ) በፕሮፌሰር ክሽችኖቢች ይመልከቱ ።

14 በቅድሚያ የተዘጋጀ የልደት የምስክር ወረቀትም ሆነ ሀ ከ ለ ለመወለዱ ቀጥተኛ ማስረጃ አስፈላጊ አይደለም (ከላይ ስለአመሠራረት የተጻፈውን ይመልከቱ) ።

15 በተለመደው ሁኔታ እንደልጅ ተደርጎ መያዙና እንደልጅ ተደርጎ መታወቁ ። በኢትዮጵያ የቤተሰብ ስም ባለመኖሩ የመጀመሪያው የተለመደ ሁኔታ ፣ ስም ፣ ለኢትዮጵያ ሕግ አሠራር አያገለግልም ።

16 ሁሉም በፍርድ ቤት ውሳኔ የተሰጠባቸው ጉዳዮች በሕግ ፋኩልቲ የማይታተሙ ወይም የማይመዘገቡ መሆናቸውን ማወቅ ይገባል ።

17 “አከራካሪ” ሲባል በልጅነት ሁኔታ መኖር ሳይሆን በሌሎች ቀዳሚ ሁኔታዎች የእናትና የልጅ ግንኙነት መኖሩን በማረጋገጥ የሚቀርብን ክስ ለማመልከት ነው ።

18 በፈረንሳይኛ “አክሲዮን አን ሪሰርሽ ደ ማተርንቴ”

19 ከትርጉም ስህተት የተነሳ የእንግሊዝኛው ቅጅ በአመልካችነት ሊቀርቡ የሚችሉ ልጆች ብቻ እንደሆኑ ያስመስላል ። እናትም (አባትም) ሊሆኑ እንደሚችሉ አንቀጽ ፯፻፸፩ (፪) ያመለክታል ።

20 ይህ አመለካከት ትክክል ነው ። በንብረት ሕግም ሆነ (ተንቀሳቃሽ ንብረት አንቀጽ ፩ሺ፩፻፺፫) በመውለድ ሕግ (አንቀጽ ፯፻፳) ፣ ባለእጅ ወይም ባለይዞታ የሆነው ሰው “መጠየቅ” ሳያስፈልገው ፣ ባለእጅ ወይም ባለይዞታ መሆኑ ብቻ ባለመብት ለመሆኑ ማረጋገጫ ነው ።

21 በዚህ ረገድ “ስለባለሥልጣን ጽሑፍ” አሰጣጥ በአንቀጽ ፯፻፸፪ የተመለከተው ፣ የግርጌ ማስታወሻ ቁጥር 12 በሚያብራራው የዚህ ጽሑፍ ክፍል በቀረበው ማብራሪያ ምክንያት ሊሠራ አይችልም ።

22 ከላይ ይመልከቱ ።

23 ለተጨማሪ ማብራሪያ የቀድሞውን ሪፖርት ገጽ 521 ይመልከቱ ።

24 እዚህ ላይ ክርክር የሚቀርብበት የእናትነት ሁኔታ በመኖሩ ላይ ሳይሆን በዚህ ሁኔታ መኖር መብት ላይ መሆኑን ማስታወስ ተገቢ ነው ።

25 ስለ አባትነት ሙሉ በሙሉ እርግጠኛ ለመሆን አለመቻሉ በሚገባ የሚታወቅ ከመሆኑም ሌላ ።

እናትንትን ለማስረዳት እንዳደረግነው ሁሉ አሁንም ፤

(፩) አመሠራረቱን (፪) የማያከራክር ማስረጃን (፫) አከራካሪ ማስረጃን እና (፬) ክርክርን በቅደም ተከተል እንመለከታለን ።

## ፩/ አመሠራረት

እናት አንድን ልጅ በቀጥታ አርግዛ የምትወልድ በመሆኑ እናትንትን በመወለድ ማረጋገጥ የሚቻል ሲሆን ፣ አባት ግን በተመሳሳይ ሁኔታ የማይወልድ በመሆኑ ፣ አባትነትን በተመሳሳይ መንገድ ማረጋገጥ አይቻልም ። መወለድን "በተፈጥሮ ሐቅ" የማስረዳትን ዘዴ ደጋፊዎች እንኳን ቢሆኑ ፣ መወለድን ለማረጋገጥ ብዙ ጊዜ የሚጠቀሙት ሰውየው አባት ሊሆን የሚችል መሆኑን በሚያመለክቱት በሕጋዊ "ግምት" ወይም "አባትነትን በማወቅ" ነው ። እነዚህ ሁለት ዘዴዎች ሥር ሰደው የሚገኙት "ከተፈጥሮ ሐቅ" ሁኔታዎች[26] ይልቅ ከጥንት ጀምሮ በባልና ሚስት መካከል "የመተማመን ግዴታ" ወይም "ተስማምቶ መቀበል" መወለድን[27] በማረጋገጥ ረገድ አመዝነው በሚታዩባቸው ሕብረተ ሰቦች ነው ። የኢትዮጵያ ሕግ በነዚህ በሁለቱ አመለካከቶች መካከል ያለው የቲዎሪ ውዝግብ ሳያግደው የራሱን የተለየ አቋም ይዞ ይገኛል ። ቀጥሎ እንደሚታየው ሁለቱም አመለካከቶች ቢሆኑ ለኢትዮጵያ ሕግ አሠራር ሙሉ መፍትሔ ሊሰጡ አይችሉም ።

በኢትዮጵያ የአባትነት አመሠራረት ዓይነቶች ከዚህ የሚከተሉት ናቸው ፤—

(ሀ) ሕጋዊ ግምት (ለ) አባትነትን ማወቅ (ሐ) አንዳንድ ጊዜም በፍርድ የሚደረግ አባትነትን ማወቅ ፡

## ፩ ፤ ሀ/ ሕጋዊ ግምት[28]

### (፩) መሠረቱ

በብዙ የሰለጠኑ አገሮች የሚሠራበት "በጋብቻ የተሳሰረ አባት ነው"[29] የሚለው ሕጋዊ ግምት የኢትዮጵያ ሕግ አካል ነው (አንቀጽ ፯፻፵፩) ። ይሁን እንጂ በኢትዮጵያ ይህ ሕጋዊ ግምት ሰፋ በማለት ከጋብቻ ውጭ እንደባልና ሚስት የሚኖርንም ይጨምራል (አንቀጽ ፯፻፵፮) ። ስለሆነም በኢትዮጵያ ይህ ሕጋዊ ግምት ፡ "በጋብቻ የተሳሰረም ሆነ ከጋብቻ ውጭ እንደባል የሚኖር አባት ነው" ሊባል ይችላል ማለት ነው ። ዝቅ ብሎ እንደሚገለጸው[30] ይህ ሕጋዊ ግምት ብዙውን ጊዜ ሊለወጥ (ሊፈርስ) የማይችል በመሆኑ (አንቀጽ ፹፬)[31] ፣ በጋብቻም ሆነ ከጋብቻ ውጭ እንደ ባልና ሚስት መኖር[32] በነዚህ ሁኔታዎች የተረገዘና የተወለደን ልጅ አባትነት በማስረዳት ረገድ ተመሳሳይ ናቸው ። ይህ ሁኔታ ከተሟላ አባትነት በቀጥታ "ከእናትነት" መረጋገጥ ይገ (ከላይ ይመልከቱ) ፡

### (፪) የተለየ ሁኔታ

ከላይ የተመለከተው የአባትነት ግምት ጋብቻው ከፈረሰበት ወይም ከጋብቻ ውጭ እንደባልና ሚስት መኖሩ ከቀረበት ጊዜ ጀምሮ እስከ ፻፹ ቀን ድረስ የሚወለዱትን ልጆች ይጨምራል (አንቀጽ ፯፻፵፫-፩ እና ፯፻፵፰-፪) ። ይሁን እንጂ ልጁ የተወለደው ጋብቻው ከፈረሰ ወይም እንደ ባልና ሚስት አብሮ መኖሩ ከቀረ ከ፫፻፲ ቀናት በኋላ ከሆነ ፣ የልጁ ሕጋዊ አባት አባትነቱን ልጁን ለማወቅ (ለመቀበል) ለሚፈልግ ለሌላ ሰው አሳልፎ ለመስጠት በመዋዋል የአባትነቱን ግምት ለማስቀረት እንደሚችል ተመልክቷል ።[33] ስለ ልጁ ጥቅም መጠበቅ በሕጉ በግልጽ ያልተጠቀሰ ቢሆንም ፤ የአባትነቱን መተላለፍ ፍርድ ቤት ስምምነቱን እናትዮዋን ከሰማ በኋላ የሚያጸድቀው በመሆኑ መንፈሱ የተጠበቀ ይመስላል (አንቀጽ ፯፻፷፯) ።[34]

የሁለት ሰዎች የአባትነት ግምት ሲኖር አባትነትን በውል ማስተላለፉ በሁለት በሕግ አባት ናቸው ተብለው በሚገምቱ ሰዎችም መካከል ሊደረግ ይችላል (አንቀጽ ፯፻፷፪) ። ይህ የሚፈጠረው አንደኛው ሰው በጋብቻ ምክንያት አባት እንደሆነ በሚገመትበትና ሴትዮዋ በዚሁ ጊዜ ከሌላ ሰው ጋር ከጋብቻ ውጭ እንደሚስት አብራ በመኖሯ[35] የተነሳ አባት እንደሆነ በሚገመትበት ጊዜ ነው[36] ። በሁለቱ ሰዎች መካከል የሚፈጠረውን ጥያቄ ለመፍታት የሚደረገውን ውል (የልጁን ጥቅም ለመጠበቅ ይመስላል) ፣ እናትዮዋን ከሰማ በኋላ (አንቀጽ ፯፻፷፫) ፍርድ ቤት ሊያጸድቀው ይገባል ። ጥያቄው በውል በማይፈታበት ጊዜ ቅድሚያ በጋብቻ ምክንያት አባት እንደሆነ ለሚገመተው ሰው እንዲሰጥ አንቀጽ ፯፻፷፬-ሀ ይደነግጋል ።

---

26 በግርጌ ማስታወሻ ቁጥር 6 የተጠቀሰውን አውሬሊያን ጆኔስኮን ይመልከቱ ።
27 ከጋብቻ (መተማመን) ወይም ከስምምነት (ማወቅ) እንደሚመነጩት ።
28 ሰፋ ላለ ማብራሪያ የቀድሞውን ሪፖርት ገጽ 513 ይመልከቱ ።
29 ፓተር ኤዝ ኤስት ኪዎ ኑፕታይ ዴሞንስትራንት ።
30 ከዚህ በታች አከራካሪ የልጅነት ማስረጃ የሚለውን ይመልከቱ ።
31 በተለይም እናትዮዋ ከሌላ ወንድ ጋር ግንኙነት ነበራት ብሎ በመከራከር ለማፍረስ አይቻልም (አንቀጽ ፯፻፹፬) ።
32 አንድ ወንድና አንድ ሴት የጋብቻ ውል ሳይኖራቸው እንደባልና ሚስት አብረው ሲኖሩ የሚፈጠር ሁኔታ ነው (አንቀጽ ፯፻፳) ።
33 አንቀጽ ፯፻፷፩ እና የዚህን ሪፖርት መደምደሚያ ይመልከቱ ።
34 የቀድሞውን ሪፖርት ገጽ 518 ይመልከቱ ።
35 እንዲህ ያለው ከጋብቻ ውጭ እንደባልና ሚስት መኖር በተለይም ባልየው ለረዥም ጊዜ በማይኖርበት ወይም ባልና ሚስቱ አብረው በማይኖሩበት ሁኔታ ይዘወተራል ።
36 የአባትነትን መደራረብ በሚመለከት በቀድሞው ሪፖርት ገጽ 518 የግርጌ ማስታወሻ ቁጥር 61 ሌላ ምሳሌ ተሰጧል ።

## ፩ ፲ ለ/ማወቅ

ይህ ርዕስ በቀድሞው ሪፖርት[37] በሚገባ ተብራርቶ የቀረበ ስለሆነ ፣ በዚህ ጽሑፍ ውስጥ አንዳንድ ሁኔታ ዎችን ብቻ እንመለከታለን ።

ማወቅ የልጅነት ማረጋገጫ የሚሆነው አባትነትን በሚመለከት ብቻ ነው ።

በልጅነት ሊታወቅ የሚችል ፣ በሕጋዊ ግምት ወይም ቀደም ሲል በተደረገ መታወቅ (አንቀጽ ፯፻፶፮)[38] ሕጋዊ አባት የሌለው ልጅ ብቻ ነው (አንቀጽ ፯፻፵፯) ። ይህ ሁኔታ ከላይ ከተጠቀሰው ዓይነት በስተቀር ሌላ የአባትነት መደራረብ እንዳይኖር ይከላከላል ።

አንድ ሰው አንድ ጊዜ አባትነቱን አውቆ ከተቀበለ መቀበሉ የሚያስከትለውን ውጤት የማይፈልገው ቢሆንም እንኳን ማወቁ የጸና ይሆናል ። ተቀባዩ አባትነቱን በማወቁ የተነሳ ጥቅማቸው የሚነካ[39] ቢሆንም እንኳን የአዋቂው ዘመዶች ማወቁን ለመቃወም አይችሉም ።

አባትነትን ማወቅ በጽሑፍ መደረግ ያለበት ይሁን እንጂ (አንቀጽ ፯፻፵፰) ፣ በባለሥልጣን እንዲረጋገጥ አስፈላጊ አይደለም ።

የልጁ አባት የሞተ ወይም ሐሳቡን (ፈቃዱን) ለመ ግለጽ በማይቻልበት ሁኔታ ላይ የሆነ እንደሆን የልጁ መታወቅ በአባቱ ወላጆች ሊደረግ ይችላል (አንቀጽ ፯፻፶) ።

የአባትየው ልጁን ማወቅ በእናትየዋ[40] ወይም እስዋ በሌለችበት ጊዜ በወላጆችዋ ተቀባይነት ካላገኘ በስተ ቀር ዋጋ አይኖረውም (አንቀጽ ፯፻፶፩) ። እንዲሁም የአ ባትየው ልጁን ማወቅ ልጁ አካለ መጠን የደረሰ ሆኖ ካልተቀበለው ዋጋ አይኖረውም (አንቀጽ ፯፻፶፪) ።[41] ታዋቂው ተቃውሞ እስካልሰነዘረ ድረስ መታወቁን እንደተቀበለው ይቆጠራል (አንቀጽ ፯፻፶፫) ።

ልጅ ወይም የልጅ ልጅ ተክቶ የሞተን ልጅ ማወቅ ይቻላል (አንቀጽ ፯፻፶፬) ።

ልጄ ነው ሲል አባት የሰጠውን ቃል ለመለወጥ አይ ችልም ። ሆኖም ይኸንን ቃል የሰጠው አሳዳሪው ሳይ ስማማ አካለ መጠን ያላደረሰ አባት ከሆነ ፣ ይኸንኑ ቃሉን አካለ መጠን ከደረሰ በኋላ በአንድ ዓመት ውስጥ ሊለውጥ ይችላል (አንቀጽ ፯፻፶፭) ።

ማወቁ የተደረገው ኃይል በመጠቀም ከሆነ ፈራሽ ሊሆን ይችላል ። ልጁ ልጄ ነው ብሎ የተቀበለው ሰው ልጁ ከሱ ሊጸነስ የማይችል መሆኑን በግልጽ ካላስረዳ በስተቀር ፣ በስህተት ወይም በማታለል የተደረገ ነው በማለት ለማፍረስ አይችልም (አንቀጽ ፯፻፶፮) ። ስለዚህ ታማኝነት በሌላት ወዳጁ ልጁ ያልሆነውን ልጁ አድ ርጎ በመቀበል ስህተት የፈጸመም ሆነ በመታለል ልጁ ያልሆነውን ልጁ አድርጎ የተቀበለ ሰው በኋላ ቢጸጸት[42] የመካድ ክስ ከማቅረብ በስተቀር ምንም መፍትሔ የለ ውም ማለት ነው ።

በሕጋዊ ግምትም[43] ሆነ በማወቅ የተመሠረተ ሕጋዊ አባትነት ፣ ከአባትየው በስተቀር በሌላ ሰው ክርክር ሊነሳበት አይችልም ።

## ፩ ፤ ሐ/በፍርድ ስለሚደረግ የአባትነት ማወቅ

አንድ ልጅ ሕጋዊ አባት የሌለው ሲሆንና የልጁ መጸነሻ ነው ተብሎ በሚታመነው ጊዜ ውስጥ[44] የልጁ እናት የመጠለፍ ወይም የመደፈር ሥራ ደርሶባት የወ ለደች እንደሆነ ፣ በተለየ ሁኔታ[45] "አባትነት በፍርድ እንዲታወቅ" ሊደረግ መቻሉን ሕግ ይደነግጋል (አንቀጽ ፯፻፶፰) ።

በእናትየዋ መቅረብ የሚገባው[46] የዚህ ክስ የጊዜ ገደብ ልጁ ከተወለደበት ወይም በመጥለፉ ወይም በመ ድፈሩ ሥራ ላይ የወንጀል ፍርድ ከተሰጠበት ጊዜ አን ስቶ ሁለት ዓመት ይሆናል (አንቀጽ ፯፻፶፱) ። የመጥ ለፉ ወይም የመድፈሩ ሥራ ተረጋግጦ ፍርድ ከተሰጠና ጠላፊው ወይም የመድፈሩን ሥራ ፈጻሚው ልጁ ከእሱ[47] ሊፀነስ የማይችል መሆኑን በግልጽ ሊያስረዳ ካልቻለ በስተቀር አባትነቱን በፍርድ እንዲያውቅ መደ ረግ አለበት (አንቀጽ ፯፻፷) ።

ከዚህ በላይ ለተመከተው የአባትነት ማረጋገጫ ዘዴ ያለው ምክንያት ለሌሎቹ የአባትነት ማረጋገጫ ዘዴ ዎች ካለው ምክንያት የተለየ ይመስላል ። አንድ ሴትና ወንድ አብረው ከመኖራቸው የተነሳ[48] የአባት ነት ሕጋዊ ግምት መደረጉ ፣ ወይም ይህ በማይኖርበት ጊዜ በፈቃደኝነት አባትነት መታወቁ ፣ አብዛኛውን ጊዜ በእርግጥ የአባትነቱን መኖር በይበልጥ ያመለክ ታል ፡ አባትነቱን ተገዶ እንዲቀበል በተደረገ ጠላፊ ወይም የመድፈር ሥራ ፈጻሚ ረገድ ግን ይህ እውነት

---

37 የቀድሞውን ሪፖርት ገጽ 514-517 እና የዚህን ሪፖርት መደምደሚያ ይመልከቱ ።

38 ወይም ከዚህ በላይ በልዩ ሁኔታ በ/ሁ ii ወይም ከዚህ በታች በ/ሐ ልጅነትን መወሰን ።

39 ለምሳሌ ቀለብ በመስጠት ግዴታ ወይም በውርስ ሕግ ረገድ ።

40 ይህ የእናትየዋን ማንነት በቅድሚያ ማረጋገጥን ይፈልጋል (ብዙውን ጊዜ የእናትነት ሁኔታ መኖርን በማሳየት) ። እንደምንጊዜውም ሁሉ በዚህም ሁኔታ የአባትነት መረጋገጥ ከእናትነት መረጋገጥ ይከተላል ።

41 የአካለ መጠን መድረሻ ዕድሜ ፲፰ ዓመት ነው (አንቀጽ ፩፻፺፰) ።

42 የዚህን ሪፖርት መደምደሚያ ይመልከቱ ።

43 ከታች ስለክርክር የተጻፈውን ይመልከቱ ።

44 ከመጥለፉ ወይም ከመድፈሩ ሥራ በኋላ ከ፩፻፹-፫፻ ቀናት (አንቀጽ ፯፻፵፪ እና ፯፻፵፫) ።

45 አንቀጽ ፯፻፶፰ ይመልከቱ ።

46 እናትየዋ ከሞተች ወይም ሐሳቧን ለመግለጽ በማትችልበት ሁኔታ ላይ ካለች በልጁ አሳዳሪ ።

47 ለምሳሌ ለመውለድ የማይችል መሆኑን በማሳየት ።

48 ጋብቻ ወይም ከጋብቻ ውጭ እንደባልና ሚስት መኖር ።

ሊሆን አይችልም ። ተገዶ አባትነቱን እንዲቀበል ማድረጉ ለፈጸመው የወንጀል ሥራ በተለየና[49] የግል ካሣ ዓይነት መልክ ባለው ቅጣት እንዲቀጣ ማድረግ ነው ። ይህንንም ፣ የመወለድ ውጤቶች በሁሉም ሁኔታዎች አንድ ዓይነት ናቸው ከሚለው መሠረተ ሐሳብ ውጭ ፣ በዚህ ሁኔታ አባትነቱን እንዲቀበል የተደረገው አባት ልጁን ሊያሳድገውና ሊደግፈው ግዴታ ያለበት ሆኖ ሳለ (አንቀጽ ፯፻፹-፩) ፣ ልጁ ግን በዚህ ሁኔታ የተቀበለውን አባቱን "የመጦር" ግዴታ የሌለበት በመሆኑ (አንቀጽ ፯፻፲) ለመገንዘብ ይቻላል ።[50]

የጠለፋ ወይም የመድፈር ሥራ ካልተፈጸመ በስተቀር አባትነት በፍርድ እንዲታወቅ ማድረግም ሆነ እንዲደረግ መጠየቅ አይቻልም (አንቀጽ ፸፯)[51] ። ይህ ገደብ ፣ በጋብቻ ወይም ከጋብቻ ውጭ እንደባልና ሚስት አብረው ከሚኖሩ በስተቀር ፣ በአንድ ሴትና በአንድ ወንድ መካከል ያሉ ሌሎች ግንኙነቶች ሕጋዊ ውጤት የሌላቸው መሆኑን በሚገልጸው በአንቀጽ ፯፻፰፩ በተጨማሪ የተደገፈ ነው ። ከእነዚህ ሌሎች ግንኙነቶች ("አንዳንድ ጊዜ" የሚደርሱ) የሚወለዱ ልጆች ሕጋዊ መተሳሰር ያላቸው ከእናትዮዋ ጋር ብቻ ነው ።[52] የሚመለከታቸው ወገኖችም ሆነ ሌሎች ለማንኛውም ጉዳይ ቢሆን (ለምሳሌ ጥፋት በሌለበት ሁኔታ ከውል ውጭ በሆነ ግዴታ ካሣ ለመጠየቅ) እነኝህን ግንኙነቶች በማንሳት በፍርድ ቤት ሊጠቀሙባቸው አይችሉም በሚል የተደነገገው[53] ይህን ገደብ ይበልጥ ያጠነክረዋል ።[54]

በመጀመሪያ የተጠቀሱት ገደቦች ከ፲፱፻፲፪ ዓ/ም በፊት የነበረውን "አባትነትን መፈለግ የተከለከለ ነው" የሚለውን የፈረንሳይ ሕግ መሠረተ ሐሳብ[55] በጉልህ ያንፀባርቃሉ ።[56] ይህ አመለካከት በአሁኑ ጊዜ ብዙ አገሮች[57] አባትነትን መፈለግ እንዲቻል ሰፋ ያለ መንገድ[58] በመክፈት ከወሰዱት አዝማሚያ የሚቃረን ሆኖ ይታያል ። ከ፲፱፻፳ ዓ/ም በፊት በኢትዮጵያ አባትነትን የመፈለጊያ መንገዶች ሰፊ ነበሩ ። የአሁኖቹ ገደቦች "ለመውረስ ዓላማ ብቻ መወለድን ለማረጋገጥ የሚቀርቡ መሠረተ ቢስ ክሶችን" ለማስቀረት የተደረጉ ናቸው ።[59] እነዚህ ገደቦች ባሕላዊ ልምዶችን ስለሚቃረኑ አንዳንድ ጊዜ የሚያልፉዋቸው ፍርድ ቤቶች አይታጡም ። ስለዚህ በኢትዮጵያ ውስጥ የመወለድን ሕግ በሚመለከት ረገድ በፍርድ ቤቶች በኩል (ሕጉን በማላላት) ቀድሞ ወደነበረው ሁኔታ የመመለስ አዝማሚያ ይታያል ። በሕጉ ውስጥ የተተከረባቸውን ጽንሰ ሐሳቦችና የሕጉን አቀራረብ በሚገባ አለመረዳት ለዚህ አመች ሁኔታን ፈጥሮዋል ። በተለይም አብዛኛውን ጊዜ ፍርድ ቤቶች ፣ በአባትነት አመሠራረት ዘዴዎችና (ለምሳሌ ማወቅ) በአባትነት ማስረጃ ዘዴዎች (ለምሳሌ የሁኔታ መኖር) መካከል ልዩነት አያደርጉም ።

## ፪/ የማያከራክር[60] ማስረጃ

ቀደም ሲል እናትነትን በማስረዳት ረገድ ስለማያከራክር ማስረጃ ሲወሳ በተጠቆሙት ምክንያቶች ፣ አባትነትንም በቅድሚያ በተዘጋጀ "የልደት የምስክር ወረቀት" (እንደሕጉ ትርጉም) ወይም "በታወቁ ጽሑፎች" አማካይነት ለማስረዳት የማይቻል ስለሆነ ፣ ብቸኛና ትክክለኛ የሆነው የማያጠራጥር የአባትነት ማረጋገጫ ዘዴ ፣ የልጅነት ሁኔታ መኖር ነው ።

ይህ ሁኔታ በሕጋዊ የአባትነት ግምት[61] እና በማወቅ[62] ረገድ የመወለድ ማረጋገጫ ዘዴዎች ያላቸው ድክመት የሚያስከትለውን ውጤት በጣም ይቀንሰዋል ። አንድ ልጅ በአንድ ሰው ፣ በሰውየው ዘመዶችና በሕብረተሰቡ እንደሰውየው ልጅ ተደርጎ ከተቆጠረና (አንቀጽ ፯፻፸-፪) ሰውየው ያለጉዛዜ ከሞተ ፣ ልጁ ወራሽነቱን ለማረጋገጥ የሚያስፈልገው በሚመለከታቸው ሁሉ እንደልጅ ተደርጎ መቆጠሩን በአራት ምስክሮች ማረጋገጥ ብቻ ነው (አንቀጽ ፯፻፸፩-፩) ።[63] ከዚህ በኋላ ማንም ተቃዋሚ ቢሆን በቅድሚያ በአራት ምስክሮች (አንቀጽ ፯፻፸፩-፪) ልጁ "የልጅነት ሁኔታ" የሌለው መሆኑን ለማረጋገጥ ካልቻለ በስተቀር ፣ ልጁ ልጅነቱን

---

49 በአንቀጽ ፪ሺ፴፩ እና ፪ሺ፶፯ ላይ ያልተመሠረተ ።

50 ሬኔ ዳቪድ ፣ ሉ ድርዋት ዱ ላ ፋሚል ዳን ሉ ኮድ ሲቪል ኢትዮፒን ፣ ሚላኖ ፣ ጉፍሬ ፣ 1967 ፣ ገጽ 66

51 ይህ ሁኔታ በጋብቻ ፣ ከጋብቻ ውጭ እንደባልና ሚስት በመኖር ወይም በማወቅ የተረጋገጠ አባትነት "በፍርድ እንዲታወቅ የተደረገ አባትነት" አለመሆኑን እንድንቀበል ያስገድደናል ።

52 ሆኖም በኋላ የሚደረገን የማወቅ ውጤት አያስቀረውም ።

53 ከፈረንሳይ ሕግ አሠራር የሚቃረን ይመስላል (በግርጌ ማስታወሻ ቁጥር 56 የተጠቀሰውን ይመልከቱ) ።

54 ጆርጅ ክሸችኖቢች ፣ "የፍትሐ ብሔር ሕግ ቁጥር 758-761 ፣" የኢትዮጵያ ሕግ መጽሔት ቮልዩም ፪ (፲፱፻፷፭) ፣ ገጽ 185 እንዲሁም አንቀጽ ፩፻፹፱ ይመልከቱ ።

55 "የኖቬምበር ፲፪ ፲፱፻፲፪ ዓ/ም" የፈረንሳይ ሕግ በዚህ ረገድ ያለውን አመለካከት አሻሽሎታል ። እንዲሁም በቅርቡ "በጃንዋሪ ፫ ፲፱፻፸፪ ዓ/ም ሕግ" የበለጠ መሻሻል ተገኝቷል ።

56 በጠለፋና በመድፈር ሥራ ሳቢያ ከሚሆነው በስተቀር ። ከዚያ ወዲህ ስለተደረጉ ለውጦች ፣ ጀ ቫይዳል ፣ ለ ኢቮሉሲዮን ዱ ላ ሌጅስላሲዮን ሱር ላ ፊሊየሽን ናቱሬል ፣ (ፓሪስ ፣ ኩጃስ ፣ ፲፱፻፷፯) ይመልከቱ ። እንዲሁም ስለ ፲፱፻፸፪ ዓ/ም ሕግ ፣ ዳንት ኤንድ ሰፒተሪ ፣ ለ ነቮ ድርዋ ደ ላ ፊሊየሽን ላይብራሪ ቴክኒክ ፣ ፲፱፻፸፪ ይመልከቱ ።

57 በ፲፱፻፷፮ ዓ/ም በአውሬሊያን ጆናስኮ ተገልጾአል (በግርጌ ማስታወሻ ቁጥር 6 ተጠቅሶአል) ።

58 ለምሳሌ በማሳት አስወሰደ ተብሎ ሲጠየቅ ወይም በሌላ ሁኔታ አባትነቱን ሲያምን ።

59 የዚህን ጽሑፍ መደምደሚያ ይመልከቱ ።

60 ለዚህ ቃል ትርጉም የግርጌ ማስታወሻ ቁጥር 7 ይመልከቱ ።

61 ጋብቻን ወይም ከጋብቻ ውጭ እንደባልና ሚስት አብሮ መኖርን በሚመለከት ።

62 በጠለፋ ወይም በመድፈር ሥራ (አንቀጽ ፯፻፶፰) አባትነት በሕግ የሚመሠረትበት ሁኔታ በጣም ጥቂት ነው ፣ በዚህ ረገድ ፍርድ ቤት የሚቀርብ ጉዳይ የለም (በባሕልና በልምድ የዚህ ውጤት ብዙ ጊዜ ጋብቻ ሲሆን አንዳንድ ጊዜ ደግሞ የበቀል እርምጃ ወይም ቅጣት ይሆናል) ። ሆኖም በአንቀጽ ፯፻፳፮ የተመለከተውንና በግርጌ ማስታወሻ ቁጥር 38 የተጠቀሰውን የተለየ የአባትነት አመሠራረት ዘዴ መገንዘብ ይገባል ።

63 እንዲሁም ብዙ ጊዜ ፍርድ ቤቶች የሚቀርቡት ምስክሮች እያንዳንዳቸው ለልጅነት ሁኔታ መኖር አስፈላጊ የሆኑትን ሁኔታዎች በሙሉ እንዲያረጋግጡ የማያስገድዱ ስለሆነ ፣ እንዲሟላ የሚጠይቀውን ይቀንሱታል ።

በአባትነት አመሠራረት ዘዴዎች እንዲያረጋግጥ ሊያ ደርገው አይችልም ። ተቃዋሚው በዚህ ሁኔታ ካረጋገጠ ብቻ ነው ልጁ በሕጉ መሠረት እንደ "ማወቅ" ያሉትን የመወለድ ማረጋገጫ ዘዴዎች በመጠቀም ልጅነቱን ማስረዳት የሚገባው ። ፍርድ ቤቶች አንዳንድ ጊዜ በነዚህ ሁለት ደረጃዎች መካከል ያለውን ልዩነት አይረዱም ። በአንጻሩ ግን "ማወቅ" አለ ሲያሰኙ የሚችሉት ሕጋዊ ሁኔታዎች በሙሉ ሳይሟሉ ፤ ለምሳሌ ሰውየው ብቻ ልጁን እንደልጅ አድርጎ መቁጠሩን ብቻ "ለልጅነት ሁኔታ"[64] እንደበቂ ማስረጃ በመቁጠር ለልጁ ሲያደሉ ይታያል ።

"ለመሆኑ እናቱ ያልታወቀች ልጅ የልጅነት ሁኔታ በመኖሩ ብቻ አባቱ እንዲታወቅለት እንዲያረጋግጥ ሊፈቀድለት ይችላል ወይ ?"[65] በቀድሞው ሪፖርት እንዳብራራሁት የዚህ መቻል ትርጉም የለሽ ይመስላል ። ይሁን እንጂ በአንቀጽ ፯፻፳-፪[66] አጻጻፍ ይህን ማድረግ በግልጽ የተከለከለ አይደለም ።

## ፫/ አከራካሪ[67] ማስረጃ

የልጅነት ሁኔታ የሌለው ልጅ አባትነትን[68] ለመጠየቅ ሲፈልግ ፤

ሀ/ በጋብቻ የተፀነሰ ወይም የተወለደ መሆኑን ፤ ወይም

ለ/ ከጋብቻ ውጭ እንደባልና ሚስት በመኖር የተፀነሰ ወይም የተወለደ መሆኑን ፤ ወይም

ሐ/ የታወቀ መሆኑን የሚያስረዱ የመወለድ ሁኔታዎች መኖራቸውን ማረጋገጥ አለበት ።[69]

እናትነትን በሚመለከት የመወለድ ሁኔታዎች በማናቸውም ዘዴ ሊረጋገጡ የሚችሉ ሲሆኑ ፣ ጋብቻን ፣ ከጋብቻ ውጭ እንደ ባልና ሚስት አብሮ መኖርንና መታወቅን በሚመለከት ግን ይኸንኑ ለማረጋገጥ የሚቻልባቸው በትክክል ሥራ ላይ መዋላቸው ለአከራካሪ የልጅነት ማስረጃ መሠረት የሆኑ የየራሳቸው የማረጋገጫ ዘዴዎች አሏቸው ።

### ፫-ሀ/ ጋብቻ

"የጋብቻ የምስክር ወረቀት" (በሕጉ መሠረት)[70] ወይም "የታወቁ ጽሑፎች" ቀደም ሲል በቀረቡት ምክንያቶች ለመወለድ ማረጋገጫ ሊሆኑ እንደማይችሉ ሁሉ ፤ ለጋብቻም እንደዚሁ በሕግም ሆነ (አንቀጽ ፫፻፫፻፳፩-፩) በሌላ ሁኔታ (አንቀጽ ፫፻፫፻፳፩-፪) ማረጋገጫ ሊሆኑ አይችሉም ። ይህም "የባልና የሚስትነትን ሁኔታ መኖር"[71] (በባልና በሚስት መካከል) ብቸኛና ትክክለኛ የሆነ የማያከራክር የጋብቻ ማረጋገጫ ዘዴ እንዲሆን ያደረገው ይመስላል ።

ይህም ሲባል ፤[72] የባልና የሚስትነቱ ሁኔታ መኖር ልጁ ከሚወለድበት ወይም ከሚጸነስበት ሕጋዊ ጊዜ ጋር የተያያዘ መሆን አለበት (አንቀጽ ፯፻፵፫) ። በልጁ እናትና የልጁ አባት በተባለው ሰው መካከል ክርክር ያልተነሳበት የባልና የሚስትነት ሁኔታ[73] ከሌለ (አንቀጽ ፯፻) ፤ ጠያቂው ወገን (ልጅ ወይም አባት-አንቀጽ ፯፻፫፩) በጉዳዩ ለመቀጠል በቅድሚያ የፍርድ ቤት ፈቃድ[74] ማግኘት ይገባዋል ። የፍርድ ቤት ፈቃድ ካገኘ በኋላ ጋብቻው መፈጸሙን ማረጋገጥ ይችላል (አንቀጽ ፯፻፫፯-፯፻፹) ። አባትነትን ለማስረዳት በሚቀርብ ክስ ፣ ጋብቻው ልጁ ከመጸነሱ ወይም ከመወለዱ በፊት የተፈጸመ መሆኑን ማስረዳት ያስፈልጋል ። በሌላ በኩል ግን ልጁ ከመጸነሱ ወይም ከመወለዱ በፊት ጋብቻው ፈርሶአል የሚባል እንደሆነ ይኸንኑ የማስረዳቱ ኃላፊነት የተከሳሹ ነው ። የጋብቻ መፍረስ በጋብቻው ጊዜ የተገኘውን የመወለድ ግንኙነት ወይም መተሳሰር የማይለውጠው መሆኑን መግለጹ ተገቢ ይመስላል ።[75]

### ፫-ለ/ ከጋብቻ ውጭ እንደባልና ሚስት መኖር

እንደጋብቻ ሁሉ (የምስክር ወረቀት ያለመኖሩ ሳይነሳ ) ከጋብቻ ውጭ እንደባልና ሚስት አብሮ ለመኖርም የማያከራክር ማስረጃው የዚሁ ሁኔታ መኖር ነው ።[76] በሁለቱም ሁኔታዎች የሚገ

---

64 ለምሳሌ እንደልጅ ተደርጎ ለማይያዝና ለማይታይ ልጅ ለመኖሪያና መማሪያ የሚያስፈልገውን ወጭ በመክፈል ።

65 የቀድሞውን ሪፖርት ገጽ 520 ይመልከቱ ።

66 "በአንድ ሰው ወይም በአንዲት ሴት እንደልጅ ተደርጎ መያዙ" የሚለውን ይመልከቱ ።

67 ለዚህ ቃል ትርጉም የማርጌ ማስታወሻ ቁጥር 17 ይመልከቱ ።

68 አመዛጋቢ የሆነውንና በልጅ የሚቀርብ የመወለድ ጥያቄ መቅረብ ያለበት በእናትየዋ ላይ ነው የሚለውን የአንቀጽ ፯፻፸፮-፪ ትርጉም በሚመለከት "ስለኢትዮጵያ የቤተሰብ ሕግ አንዳንድ ጥያቄዎች" የኢትዮጵያ የሕግ መጽሔት ቮልዩም 9 ገጽ 207 እና "የቤተሰብ ሕግ ጥያቄ" ቁጥር 24 (ሕግ ፋኩልቲ ፣ አዲስ አበባ) በፕሮፌሰር ክሽችኖቢች ይመልከቱ ።

69 በኢትዮጵያ ሕግ አባትን መፈለጊያ ዘዴዎች ሰፊ አይደሉም ። በአንዳንድ አባትን መፈለጊያ ዘዴዎች ሰፊ በሆኑባቸው አገሮች ይኸው የሚመሠረተው በቅድሚያ ለምሳሌ ማሳሳት የተፈጸመ መሆኑ ወይም የታመነ መሆኑ ሲረጋገጥ ነው (በማርጌ ማስታወሻ ቁጥር 56 የተጠቀሰውን ጀ ቫይዳልን ይመልከቱ ።) በኢትዮጵያ የአባትነት ማረጋገጫ ዘዴዎች በሕግ የተወሰኑ ናቸው ።

70 አንቀጽ ፯፻፺፭ ይመልከቱ ።

71 በመወለድ ሕግ በሚደረገው ዓይነት የሚተረጉምና በዚያው ሁኔታ የሚረጋገጥ ወይም የሚፈርስ (አንቀጽ ፯፻፺፮-፺፯)

72 በ"አከራካሪ" የልጅነት ማስረጃ አባትነትን ማስረዳት ለሆነው ።

73 አንቀጽ ፯፻፩ ፣ ቀደም ሲል በተሰጡት ምክንያቶች (የማርጌ ማስታወሻ ቁጥር 12 የሚያብራራውን ክፍል ይመልከቱ) ፤ ከአሁን ወዲያ በዚህ ጽሑፍ ውስጥ "የታወቁ ጽሑፎች" አይጠቀሱም ።

74 የሃይማኖት የጋብቻ የምስክር ወረቀትን (አንቀጽ ፮፻፸፱) ፤ "የጋብቻ ውልን" (አንቀጽ ፯፻፹፫-፩) ፣ ወይም ጠንካራ የሆኑ የአካባቢ ማስረጃዎችን መሠረት በማድረግ ።

75 አንቀጽ ፯፻፺፯-፫ እና በዚህ እትም ውስጥ የሚገኘውን የጆ. ክሽችኖቢች የፍርድ ትችት ያገናዝቡ ።

76 በእኔ አስተያየት ከጋብቻ ውጭ እንደባልና ሚስት አብሮ መኖርን ለማረጋገጥ የሁኔታን መኖር መጠየቁ ማረጋገጡን በጣም ከባድ ስለሚያደርገው አስፈላጊ አይመስለኝም ። የኢትዮጵያ ቤተሰብ ሕግ ጥያቄ ቁጥር 17 (አዲስ አበባ ፣ ሕግ ፋኩልቲ) ጆ ክሽችኖቢች ይመልከቱ ።

ኘው መወለድ የሚያስከትለው ውጤት አንድ በመሆኑ ፣ ለዚህ ጽሑፍ ዓላማ ሁለቱ ሰዎች በሕግ ባልና ሚስት ሆነው መኖራቸውን (አንቀጽ ፯፻፶፱) ወይም ሳይጋቡ እንደ ባልና ሚስት አብረው (አንቀጽ ፯፻፲፰) መኖራቸውን ለይቶ ማስረዳቱ አስፈላጊ አይደለም ።[77] ይልቁንስ አስፈላጊው ጉዳይ አብሮ መኖሩ ከልጁ መወለጃ ወይም ሕጋዊ መነፀሻ ጊዜ ጋር የተያያዘ መሆኑ ነው ።

ሕግ አውጭው በዚህ ደረጃ ላይ ማቆም ሲገባው ፣ ከጋብቻ ውጭ እንደባልና ሚስት በመኖር ሁኔታ ላይ (አንቀጽ ፯፻፳ እና ፯፻፲፰) ክርክር ሲነሳበትና አራት ምስክሮች ቀርበው ስለአለመኖሩ ሲመሰክሩ (አንቀጽ ፯፻፶፱) ሁኔታው ስለመኖሩ ለማስረዳት የሚቻልበትን ሁለተኛ መንገድ በአንቀጽ ፯፻፳ ደንግጓል (ይህ በጋብቻ ሁኔታ መኖር ላይ ክርክር ሲነሳ የሚደረገውን የማስረጃ አቀራረብ ሥርዓት ያላግባብ በመከተል የተነደፈ ነው ፣ - አንቀጽ ፯፻፬-፯፻፯) ። ይሁን እንጅ ይህ አንቀጽ በሥራ ላይ ሊውል የማይችል በመሆኑ ፍርድ ቤቶች አይጠቀሙበትም ።[78]

## ፫-ሐ/ ማወቅ

አባትነትን ማወቅ በጽሑፍ መደረግ ያለበት ሲሆን፣ "በምስክሮች ሊረጋገጥ አይችልም"[79] (አንቀጽ ፯፻፵፰) ። ማወቅን ለማስረዳት ጽሑፉ ራሱ በማስረጃነት መቅረብ ይኖርበታል ።[80] በአንቀጽ ፩፻፵፯ የተገለጸውን "የታወቁ ጽሑፎችን" አሠራር በማገናዘብ የተጠቀመው ልዩ ሁኔታ ቀደም ሲል በቀረቡት አጠቃላይ ምክንያቶች የሚሠራ አይመስልም ።[81]

## ፬/ ክርክር

በጋብቻ ወይም ከጋብቻ ውጭ እንደባልና ሚስት አብሮ በመኖር[82] በሚመሠረት አባትነት ላይ ክርክር ሊነሳ የሚችለው በሕጋዊ አባትየው በራሱ[83] ብቻ እና በቀድሞው ሪፖርት በተገለጹት ምክንያቶች ብቻ ነው ። አብዛኛውን ጊዜ እነዚህ ምክንያቶች ሰውየው በልጁ ሕጋዊ የመፀነሻ ጊዜ ሁሉ ከእናትየዋ ጋር ለመገናኘት አለመቻሉ (አንቀጽ ፯፻፸፫) ወይም ልጁ ፈጽሞ ከሱ ሊወለድ የማይችል መሆኑ (ለምሳሌ ለመውለድ የማይችል በመሆኑ) ናቸው (አንቀጽ ፯፻፸፭) ።[84] እናትየዋ ከሌላ ወንድ ጋር ግንኙነት ማድረጓ ወይም እምነት አጉድላ ልጁን ከሌላ ሰው የወለደችው መሆኗን ማመኗ አባትነትን ለመቃወም በቂ ምክንያቶች አይደሉም (አንቀጽ ፯፻፸፰) ።

በአንድ በታወቀ ከጋብቻ በመነጨ የአባትነት ጉዳይ አባት የተባለው ሰው የተከላሸ ለመሆኑ የሕክምና የምስክር ወረቀት ቢቀርብም ፣ አባትየው እያለ ልጄ አይደለም ያላላውን ልጅ እሱ ከሞተ በኋላ ልጁ አይደለም በማለት የቀረበውን ክርክር የከፍተኛው ፍርድ ቤት በተገቢ ሁኔታ ውድቅ አድርጎታል ።[85]

## ሐ/ የመወለድ ውጤቶች

በማንኛውም ሁኔታ ቢመሠረትም የሕጋዊ መወለድ ውጤቶች ለሁሉም ልጆች አንድ ናቸው ።[86] ለምሳሌ ሁሉም ልጆች ከአባትየው ወይም ከእናትየዋ ቀለብ የማግኘትም ሆነ (አንቀጽ ፰፻፰-፪) አባትየውን ወይም እናትየዋን የመውረስ (አንቀጽ ፰፻፵፪) መብታቸው እኩል ነው ።

በአንጻሩ ግን በሕግ ያልተመሠረተ ሆኖም ግን ግልጽ የሆነ የዲቃላ ልጅነት ጋብቻን በማስከልከል ረገድ[87] ብቻ በቂ የመሆን ውጤት አለው (አንቀጽ ፭፻፹፬) ።

### መደምደሚያ

፩/ በጋብቻም ሆነ ከጋብቻ ውጭ የተወለዱ ልጆችን በሚመለከት ረገድ በውጭ ሀገሮች የሚደረጉ አዳዲስ የሕግ ለውጦች አንዳንዶቹ በቅርቡ ሕጋዊ እኩልነትን ያስገኙ ሲሆን ፣ ሌሎቹ ደግሞ ቀስ በቀስ ይህን እኩልነት ለማምጣት በመሞከር ላይ ናቸው ። ይህ እኩልነት በኢትዮጵያ ውስጥ ሥር ሰዶ የቆየ ነው ።

፪/ በጋብቻና ከጋብቻ ውጭ የተወለዱ ልጆችን ሕጋዊ እኩልነት በተግባር ለመተርጎም የመወለድ ግንኙነቶች የሚረጋገጡባቸውን ዘዴዎች ሰፋ ማድረግ ያስፈልጋል ። ይህን አመለካከትና አቅጣጫ የውጭ ሀገሮች የሕግ አሻሻዮች የሚከተሉት ይመስላል ። በዚህ ረገድ ኢትዮጵያ የተለየ አቅጣጫ ስትከተል

---

77 የበላይነት በሌለው በዚህ አንቀጽ (እና በአንቀጽ ፯፻፳) የእንግሊዝኛ ቅጅ ሳይጋቡ እንደባልና ሚስት መባሉ ቀርቶ እንደባልና ሚስት ስለተባለ ልዩነቱን መገንዘብ የበለጠ አስቸጋሪ ነው ።

78 የቤተሰብ ሕግ ጥያቄዎች ቁጥር 18 (አዲስ አበባ ፣ ሕግ ፋኩልቲ) በጆ. ከሸችኖቢች ይመልከቱ ።

79 ለምሳሌ አይተነዋል ወይም በአንቀጽ ፩ሺ፯፻፳፯(፪) መሠረት በፊርማችን አጽድቀነዋል በሚሉ ።

80 ስለሆነም እነዚህን መሰል ሰነዶችን በፍርድ ቤት ማስመዝገብ ይጠቅማል ።

81 እንዲሁም ይህ ማገናዘብ ከአንቀጽ ፩፻፵፯ መንፈስ ጋር የማይጣጣም በመሆኑ ።

82 አንቀጽ ፯፻፸፩ "ራሱ ለአወቀ" አባት የሚሠራ ቢሆንም ፣ ከአንቀጽ ፯፻፵፰-፪ ጋር ይጋጫል ።

83 "ልጄ አይደለም" በማለት የሚቀርብ ክስ ።

84 ሌላው ምክንያት ደግሞ ክርክሩን ከሚያቀርበው ሰው ሚስት ወይም ከጋብቻ ውጭ እንደሚስት አብራ ከምትኖር ሴት አንድ ልጅ እናትነትን በሚጠይቅበት ጊዜ የሚነሳ ነው ። ይህ ሁኔታ በአንቀጽ ፯፻፸፱ ፣ ፯፻፵፯ (፮-፫) የሚሸፈን ይመስላል ።

85 በዚህ እትም ውስጥ የሚገኘውን በጆ. ከሸችኖቢች የቀረበውን የፍርድ ግምገማ ይመልከቱ ።

86 በጠለፋ ወይም በመድፈር ሥራ ከሚመነጨው ልዩ ሁኔታ በስተቀር (ከላይ ይመልከቱ) ።

87 "ፓፕሊካይ አነስታቲስ" — ፓፕሊክ ኦነስቲ

ትታያለች ። ምክንያቱም በአንድ በኩል በጋብቻና ከጋብቻ ውጭ በተወለዱ ልጆች መካከል ያለውን ልማዳዊ እኩልነት አጥብቃ የያዘች ሲሆን ፤ በሌላ በኩል ግን ከ፲፱፻፷ ዓ/ም ወዲህ ቀደም ሲል ሰፊ የነበሩትን የመወለድን ማረጋገጫ ዘዴዎች አጥብባለችና ነው ። ለዚህ የማጥበብ እርምጃ መነሻ ምክንያቱ ለመውረስ ዓላማ ብቻ መወለድን ለማረጋገጥ የሚቀርቡ መሠረተ ቢስ ክሶችን መከላከል ነው ። ሊወረሱ የሚችሉ የግል ንብረቶች አነስተኛ በሆኑባቸው አገሮች ከላይ የተጠቀሰው ምክንያት የሚያስከትለው ተጽእኖ እምብዛም ስለሆነ ፤ በሶሻሊስት አገሮች መወለድን የማረጋገጫ ዘዴዎች ሰፊ ናቸው ። በኢትዮጵያ እነኚህ ዘዴዎች በሕግ ሰፊ ባይሆኑም ፤ በፍርድ ቤቶች የላላ አተረጓጎም ምክንያት ለቀቅ ብለው ይታያሉ (የግርጌ ማስታወሻ ቁጥሮች ፳፬-፳፭ እና የሚያብራሩትን ክፍል ይመልከቱ ።)

፫/ በኢትዮጵያ አባትነትን የማረጋገጫ ዘዴዎች የተወሰኑ ናቸው ።

ከዚህ ቀጥለን በዘጠነኛው ጠቅላላ ጉባኤ በሌሎች አገሮች ሪፖርቶች ያልተጠቆሙ የኢትዮጵያን ሕግ የተለዩ ሁኔታዎች እንጠቁማለን ፤

ሀ/ ኢትዮጵያ ከእናትዮዋ ጋር ከጋብቻ ውጭ እንደባል በሚኖር ሰው ላይ ሕጋዊና ተቃራኒ ማስረጃ ሊቀርብበት የማይችል የአባትነትን ግምት ትጥላለች ። ለዚህ ዓላማ እንዲህ ዓይነቱ ሰው እንደ ባል ይቆጠራል ።

ለ/ በኢትዮጵያ ውስጥ እናትነት ብቻ ሳይሆን አባትነትም በሁኔታ መኖር ብቻ ሊረጋገጥ ይችላል (በሕጉ የተገለጹት የመወለድ ማረጋገጫ ዘዴዎች መኖራቸውን ማሳየት ሳያስፈልግ) ። በዚህ ረገድ በሁኔታ መኖር መወለድን በማረጋገጥ እና (አንቀጽ ፯፻፹-፭-፱) የተንቀሳቃሽ ንብረቶች ባለይዞታ በመሆን ባለንብረትነትን በማረጋገጥ (አንቀጽ ፩፲ ፩፻፶፫ እና ፩፲፩፻፶፱) መካከል ግልጽ የሆነ ተመሳሳይነት አለ ።

ሐ/ ማወቅ በእናትዮዋ ተቀባይነት ማግኘት እንዳለበት በሚደነግጉ የአንዳንድ አገሮች ሕጎች ፤ እናትዮዋ ሳትቀበል ከሞተች ወይም ሐሳቧን ለመግለጽ በማትችልበት ሁኔታ ከሆነች ማወቁ ሕጋዊ ውጤት አይኖረውም ። በኢትዮጵያ ግን እናትዮዋ በዚህ ሁኔታ ብትሆንም መቀበሉ በእናትዮዋ ወላጆች ወይም በልጁ ሞግዚት ሊደረግ ይችላል ።

መ/ ኢትዮጵያ ውስጥ "በመታለል" አባትነቱን ያወቀን[88] ሰው አባትነት ፤ ማወቁን ያደረገው ሰው ራሱ አባት ሊሆን የማይችል መሆኑን በማያወላውል ሁኔታ ካላረጋገጠ በስተቀር[89] አባትነቱን ማወቁን ማፍረስ አይቻልም ።

ሠ/ በተፈጥሮ ሐቅ ወይም አንድ ሰው ያለውን ሁኔታ አሳልፎ መስጠት የለበትም በሚለው መሠረተ ሐሳብ ላይ በሚያተኩሩ አገሮች አንጻር ፤ በአንዳንድ ሁኔታዎች በኢትዮጵያ ውስጥ አባትነት ከሕጋዊ ወላጁ ልጁን ልጄ ነው ወደሚል ሌላ ሰው በውል ለማስተላለፍ ይችላል ። የሁለት ሕጋዊ አባቶች መደራረብ በሚኖርበትም ጊዜ መደራረቡ በሁለቱ አባት ተብለው በሚገመቱት ሰዎች መካከል በውል ሊፈታ ይቻላል ።

፬/ ቀደም ሲል ከተገለጸው የእኩልነት "መሠረተ ሐሳብ" ሌላ ፤ የኢትዮጵያ የመወለድ ሕግ ግልጽ የሆኑ አዝማሚያዎች እንደሚከተለው ሊጠቃለሉ ይችላሉ ፤

ሀ/ ምንም የማያከራክር የልጅነት ማስረጃ (በሁኔታ መኖር) እና በመጠኑ ሊያከራክር የሚችል[90] በመወለድ ሐቅ የሚመሠረት አከራካሪ የእናትነት ማስረጃ ፤

ለ/ ምንም የማያከራክር የአባትነት ማስረጃ (በሁኔታ መኖር) ፤

ሐ/ ፩/ አከራካሪ ማስረጃን ፤ ፪/ አባትነትንና ፫/ ከጋብቻ ውጭ ተወልደው ያልታወቁን ወይም ከጋብቻ ውጭ እንደ ባልና ሚስት በመኖር ሁኔታ ባለመወለዳቸው አባት የሌላቸውን ልጆች በሚመለከት ጠንካራ ገደብ አለው ። ከዚህ በላይ በተጠቀሙት ሦስት ማብራሪያዎች ምክንያት የእነኚህ ገደቦች ውጤት በአንቀጽ ፯፻፳፩ ከሚነበበው መለስተኛ ሆኖ ይገኛል ።

መ/ በፖሊሲ አንጻር የኢትዮጵያ መወለድ ሕግ ዓላማ የውርስ ክርክሮችን በመቀነስ ሰላማዊ ቤተሰቦች እንዲኖሩ ማድረግ ነው ።[91] ይህ ዓላማ ፤

፩/ የልጁን ጥቅም ከመጠበቅና[92] የተፈጥሮ ሐቁን ከማውጣቱ ዓላማ ጋር የተመጣጠነ ሲሆን[93] ፤

88 አንዳንድ ጊዜም "ከማከበርና ሰውን ላለማስከፋት ሲባል" ወይም በሌላ ምክንያት ማወቁ ሊደረግ ይችላል ።

89 አንቀጽ ፯፻፵፯(፪) ፤ ሆኖም ልጁ ሌላ ሕጋዊ አባት ካለው ማወቁ ከመጀመሪያው ፈራሽ ነው (አንቀጽ ፯፻፵፯) ።

90 "በመጠኑ ሊያከራክር የሚችል" መባሉ በጉዳዩ ለመቀጠል በቅድሚያ የፍርድ ቤት ፈቃድ ማግኘት አስፈላጊ መሆኑን ለመጠቆም ነው ። (አንቀጽ ፯፻፳፫-፯፻፳፬) ። ከዚያ በኋላ የመወለዱ የተፈጥሮ ሐቅ በማንኛውም መንገድ ሊረጋገጥ ይችላል (የአባትን ወላጅነት ለማረጋገጥ ይህን ማድረግ አይቻልም ።)

91 በአባትነት አመሠራረትና እንዴ ከተመሠረተ በኋላ ልጄ አይደለም በማለት ሊቀርብ በሚችል ክርክር ላይ በተጣሉት ገደቦች የተደገፈ ዓላማ ።

92 ለምሳሌ በመቀበል አስፈላጊነት (አንቀጽ ፯፻፺፭-፯፻፺፱) ወይም በፍርድ ቤት መጽደቅ አስፈላጊነት (አንቀጽ ፯፻፷፫ እና ፯፻፷፯) የተደገፈ ዓላማ ።

93 ሁለቱ ዓላማዎች ከጋብቻ ውጭ እንደባልና ሚስት በሚመሠረት አባትነት ረገድ የሚገናኙ ይመስላሉ (አንቀጽ ፯፻፴፩) ።

፪/ አንድ ሰው ያለውን ሁኔታ አሳልፎ መስጠት የለበትም[94] ከሚለው መሠረተ ሐሳብ ርቆ ይገኛል ።

## አዲስ አዝማሚያዎችን የሚጠቁም

## ተጨማሪ መግለጫ ፤ ፲፱፻፸፱ እ. ኤ. አ.

ሀ/ <u>በፍርድ ቤቶች በኩል ስላለው አዝማሚያ</u>

የመወለድ "ማረጋገጫ" ደንቦችን[95] ላላ አድርጎ በመተርጎም በመወለድ "አመሠራረት" ረገድ ያሉትን ጠበቅ ያሉ ደንቦች ላላ ባለ ሁኔታ እንዲሠራባቸው የማድረጉ አዝማሚያ ካለፉት ጥቂት ዓመታት ወዲህ በፍርድ ቤቶች አካባቢ ጎልቶ ይታያል ። በሕብረተሰብአዊት ኢትዮጵያ የመወለድ ጥያቄን ለውርስ ዓላማ የማንሳቱ አዝማሚያ እየቀነሰ የሚሄድ በመሆኑ ፤[96] በርከት ያሉት ክሶች የሚነሱት ለልጃቸው ቀለብ እንዲቆረጥላቸው በሚፈልጉ ያላገቡ እናቶች ነው ። በመወለድ ሕግ ረገድ ለወጥ ለማድረግ ከመታቀዱም[97] በፊት ቢሆን ፣ ፍርድ ቤቶች ያላገቡ እናቶች ያለባቸውን ችግር በመመልከት ፣ አባት በተባለው ሰው ላይ "ቀለብ የመስጠት" ትእዛዝ (አንቀጽ ፯፻፳፩-፩) ለማስተላለፍ ሲሉ "ለሁኔታ መኖር" ወይም /እና "ለማወቅ" አስፈላጊ የሆኑትን ሕጋዊ ሁኔታዎች ላላ አድርገው እንዲተረጉሙ ይገደዱ ነበር ። ይኸውም ከዚህ በሚከተሉት መንገዶች ይደረጋል ፤

፩/ አራቱም ምስክሮች እያንዳንዳቸው (አንቀጽ ፯፻፸፩-፩) ለሁኔታ መኖር አስፈላጊ የሆኑትን ሦስቱንም ሁኔታዎች (አንቀጽ ፯፻፸-፪) ማለትም ልጁ (፩) አባቱ በተባለው ሰው ፤ (፪) በዚሁ ሰው ዘመዶችና (፫) በሕብረተሰብ እንደልጁ ተደርጎ መታየቱን እንዲያረጋግጡ ባለመጠየቅ ፤

፪/ ማወቅ ተቀባይነት እንዲኖረው "በጽሑፍ መደረግ ያለበት" (አንቀጽ ፯፻፵፳-፩) ሆኖ ሳለ ባይሆንም ለሁኔታ መኖር አስፈላጊ ከሆኑት ሁኔታዎች መካከል የመጀመሪያው (ልጁ በሰውየው እንደልጁ ተደርጎ መታየቱ) ከተሟላ ማወቅ እንዳለ በመቁጠር ፤

፫/ <u>የሁኔታ መኖር</u> ፈራሽ ሊሆን የሚችል የአባትነት ማስረጃ ሲሆን ፣ <u>ማወቅ</u> ደግሞ ሊሻር የማይችል የአባትነት መመሥረቻ ዘዴ ሆኖ ሳለ እነዚህን ሁለት የተለያዩ ጽንሰ ሐሳቦች በማሳከርና ባለመለየት ናቸው ።

ከዚህ በላይ የተጠቆሙትን አዝማሚያዎች የሚያረጋግጡ ፍርዶችን በሌላ የዚህ መጽሔት እትም ለማቅረብ ሙከራ ይደረጋል ።

ለ/ <u>በሕግ መሻሻል ረገድ ስላሉት አዝማሚያዎች</u>

በሕግና ፍትሕ ሚኒስቴር ሥር በተቋቋመው የሕግ አሻሻይ በኩል ሕጉን ግልጽ የማድረግና ከሕብረተሰብአዊነት ፍልስፍና ጋር እንዲስማማ የማድረግ ዓላማ አለ ፤ የመጀመሪያው ደረጃ የሕግ ማሻሻሉ ሥራ በተለያዩ ንኡሳን አጥኚ ኮሚቴዎች አማካኝነት ተጠናቅቋል ። አንደኛው ንኡስ ኮሚቴ የፍትሐ ብሔር ሕግን የመጀመሪያ ሦስት መጽሐፎች የሠራ ሲሆን ፤ ይህ ጽሑፍ የሚመለከተው ክፍልም በሁለተኛው መጽሐፍ ውስጥ የሚገኝ ነው ። ከዚህ በታች "ሕግ አሻሻይ" ሲባል የፍትሐ ብሔር ሕግ ፩ኛ ፣ ፪ኛ ፣ እና ፫ኛ መጻሕፍትን ረቂቅ ያዘጋጀው (ጁን ፲፱፻፸፯ ፣ አዲስ አበባ) የሕግ አሻሻይ ፩ኛው ንኡስ ኮሚቴ ማለት ሲሆን ፤[98] "ረቂቅ ሕግ" ማለት ደግሞ ይኸው ንኡስ ኮሚቴ ያዘጋጀው የመወለድ ሕግ ረቂቅ ምዕራፍ (የአራተኛው አንቀጽ ረቂቅ አካል) ማለት ነው ።

በረቂቁ ሕግ ላይ ሰፋ ያለ ግምገማ ለማድረግ ጠለቅ ያለ ምርምር ማድረግ ያስፈልጋል ። ከዚህም በላይ የሕግ አሻሻዩ ኮሚቴ ሥራ የዋናውን ኮሚሽን አመለካከት የሚያንፀባርቅ መሆኑ ስለማይታወቅ ፣ በዚህ ደረጃ ግምገማ ማድረጉ አጉል ችኩልነት ይሆናል ። ስለዚህ በዚህ ጽሑፍ አንዳንድ መሠረታዊ ጉዳዮችን ብቻ እንመለከታለን ። የዚህ ጽሑፍ ዓላማ ከዚህ በታች የተመለከቱትን ሦስት ጥያቄዎች መመለስ ይሆናል ፤

፩/ ረቂቁ ሕግ የመወለድን ሕግ ችግሮች ምን ያህል ያቃልላል ?

፪/ ረቂቁ ሕግ ከጋብቻና ከጋብቻው ውጭ በተወለዱ ልጆች መካከል ያለውን እኩልነት ምን ያህል ይጠብቃል ?

፫/ ከጋብቻ ውጭ የተወለዱ ልጆችን ጥቅም ለመጠበቅ ፍርድ ቤቶች የሚከተሉትን ላላ ያለ የአሠራር አዝማሚያ ረቂቁ ሕግ ምን ያህል ያንፀባርቃል ወይም ይቃረናል ?

ለ — <u>፩ ማቃለል ወይም ግልጽ ማድረግ</u>

የሕግ አሻሻይ ኮሚቴው አንዱ ትልቁ አስተዋጽዖ እርስ በርሱ የሚቃረንና የተወሳሰበ ከመሆኑ የተነሳ ግልጽ ለማድረግ ችሎታ ያላቸው እንኳ ዳኞች የተቸገሩበትን የመወለድን ሕግ ማቃለሉና ግልጽ

94 አንቀጽ ፯፻፳፪ እና ፯፻፳፩ ።
95 ከላይ የመደምደሚያውን ቁጥር 2 ይመልከቱ ።
96 ከላይ የመደምደሚያውን ቁጥር 2 ይመልከቱ ።
97 ከዚህ በታች (ለ)ን ይመልከቱ ።
98 "አንቀጽ" ሲባል የፍትሐ ብሔር ሕግ አንቀጽ ማለት ሲሆን "ረቂቅ አንቀጽ" ማለት ደግሞ የረቂቁ ሕግ አንቀጽ ማለት ነው ።

ማድረጉ ነው ።[99] በረቂቁ የመወለድ ሕግ ፣ "የአባትነትን መደራረብ" የሚመለከተው ክፍል ፣ ወይም "መወለድን ማረጋገጥን" ከሚመለከተው ክፍል ብዙዎቹ አንቀጾች (አንቀጽ ፻፺፩-፻፺፫)[100] እንዲቀሩ በመደረጉ ወይም ሌሎች ክፍሎች አጠር ባለ ሁኔታ በመዘጋጀታቸው ቅር የሚሰኝ የሕግ ባለሙያ አይኖርም ።

## ለ — ፪ እኩልነት

አሁን ባለው ሕግ በጋብቻና ከጋብቻ ውጭ በተወለዱ ልጆች መካከል "እኩልነት" ያለ መሆኑን በግልጽ የሚጠቁም አንቀጽ የለም ። አባታቸው ለተረጋገጠላቸው ልጆች የዚህ መገለጽ አስፈላጊ አይደለም ምክንያቱም ፣ (፩) በቀለብ መቀበልም ሆነ (አንቀጽ ፰፻፰-፩) በውርስ ሕግ (አንቀጽ ፰፻፹፬) በሁለቱ መካከል ያለው እኩልነት የማያወላውል (ልዩነት አይደረግም) በመሆኑ እና (፪) የአባትነት አመሠራረት በጋብቻም (አንቀጽ ፯፻፵፩) ሆነ ከጋብቻ ውጭ (አንቀጽ ፯፻፵፭) ለተወለዱ ልጆች በተመሳሳይነት የሚሠራ በመሆኑ በሁለቱ መካከል ያለውን እኩልነት ስለሚያረጋግጥ ነው ። እንዲሁም (፫) ላላ ያሉትም ሆኑ (አንቀጽ ፯፻፹-፯፻፹፩) ጠበቅ ያሉት (አንቀጽ ፯፻፸፪-፯፻፸፯) የመወለድ ማረጋገጫ ደንቦች ለሁሉም ልጆች በእኩልነት የሚሠሩ ናቸው ። በነዚህ ሁሉ ምክንያቶች የእኩልነትን መሠረተ ሐሳብ በግልጽ መጠቆሙ አስፈላጊ አልነበረም ።

በአንጻሩ ረቂቁ ሕግ በጋብቻና ከጋብቻ ውጭ በተወለዱ ልጆች መካከል "እኩልነት" አለ (ረቂቁ ሕግ አንቀጽ ፪፻፺፫[101]) በማለት ይጀምርና በሚቀጥለው ክፍል (የአባትነት አመሠራረት) ግን ይኸን መሠረተ ሐሳብ በመጻረር "በጋብቻ የተወለዱ ልጆች" እና "ከጋብቻ ውጭ የተወለዱ ልጆች" በማለት በሁለት ከፋፍሎ ተመሳሳይ ባል ሆነ ሁኔታ ይመለከታቸዋል (ከታች ለ—፫—፩ ይመልከቱ) ። ይህ ክፍፍል አሁን ባለው ሕግ አሠራር ምንም አግባብ የለውም ፤ ለውጥም አያመጣም ።[102] በረቂቁ ሕግ በጋብቻና ከጋብቻ ውጭ የተወለዱ ልጆችን መወለድ በማረጋገጥ ረገድም ተመሳሳይ ባልሆነ መንገድ ይታያሉ (ከታች ለ—፫-፪ ይመልከቱ) ። ከቀለብ መቁረጥ ግዴታና ከውርስ ረቂቅ ሕግ በግልጽ (ረቂቅ ሕግ አንቀጽ ፫፻፫[103]) እንደሚታየው መወለዳቸው (ልጅነታቸው) በተረጋገጠላቸው ልጆች መካከል ያለው እኩልነት ግን እንደተጠበቀ መሆኑን መገንዘብ ይገባል ።

## ለ - ፫ ላላ ያለ አመለካከት ? ፩/ በመወለድ አመሠራረት

የመወለድን ሕግ (፩) በአመሠራረቱ (፪) በማስረዳቱ ለማላላት ይቻላል ። ሁለቱ ጽንሰ ሐሳቦች አብዛኛውን ጊዜ ተሳክረው የሚታዩ ቢሆንም ፣ ለየብቻ እንመለከታቸዋለን ።[104] ከዚህ በታች (ሀ) በሕጋዊ ግምት ፣ (ለ) በማወቅ እና (ሐ) በፍርድ እንዲታወቅ በማድረግ አባትነት እንዴት እንደሚመሠረት እንመለከታለን ።

### ሀ/ ሕጋዊ ግምት

ረቂቁ ሕግ በሕጋዊ ግምት የአባትነትን መመሥረት ቀላል ከማድረግ ይልቅ ከጋብቻ ውጭ ባሉ ሁኔታዎች[105] ሕጋዊ ግምት እንዳይሠራ በማድረግ የበለጠ አጥብቦታል (የአንቀጽ ፯፻፵፭ መንፈስ ተሠርዞአል) ።

### ለ/ ማወቅ

ፍርድ ቤቶች የረቂቁን ሕግ አንቀጽ ፪፻፷፪(፩)[106] በመተርጎም ረገድ እንደሚወስዱት አቋም ፣ በማወቅ አባትነትን መመሥረት ቀላል ወይም ከባድ ሊሆን ይችላል ። ብዙኃኑ የኢትዮጵያ ሕዝብ መጻፍና ማንበብ የማይችል በመሆኑ አብዛኛው በልማድ የሚደረግ ማወቅ በጽሑፍ አይሆንም ። በተጨማሪም አብዛኛውን ጊዜ በልማድ ማወቅ ፣ ካልተሟላ የሁኔታ መኖር እንደሚገኝ ተደርጎ ይወሰዳል (ከላይ ሀ-፪ ይመልከቱ) ። ሆኖም ይህ ልማዳዊ አመለካከት ወይም ሌሎች በጽሑፍ ያልተደረጉ ማወቆች "ተቀባይነት የሚያገኙ" ከሆነ ፣ ማወቁ የተደረገበት የጽሑፍ "ሰነድ" መቅረብ ያለበት መሆኑን የሚደነግገው ማስረጃን የሚመለከተው የረቂቁ ሕግ ክፍል (ከታች ለ-፫-፪-ለ ይመልከቱ) በሥራ ላይ ሊውል አይችልም ።

### ሐ/ በፍርድ የሚደረግ አባትነትን ማወቅ

የረቂቁ ሕግ አንቀጽ ፪፻፷፯[107] የጠለፋ ወይም

---

99 የቤተሰብ ሕግ ጥያቄዎች (አዲስ አበባ ፣ ሕግ ፋኩልቲ ፣ ፲፱፻፸፯) በጸ ክሽችኖቢች ይመልከቱ ።

100 ከላይ የተመለከተውን ቁጥር 24-25 ይመልከቱ ።

101 "አንቀጽ ፪፻፺፫. የልጆች እኩልነት:-በጋብቻ እና ከጋብቻ ውጭ በተወለዱ ልጆች መካከል ልዩነት አይደረግም ።"

102 የዚህን ሪፖርት መግቢያ ይመልከቱ ።

103 "አንቀጽ ፫፻፫. የመጀመሪያ ደረጃ ወራሾች":-

(፩) ሟችን ለመውረስ ቅድሚያ ያላቸው ልጆቹ ናቸው ።
(፪) የሟቹ ልጆች ከሟቹ ንብረት እኩል ድርሻ ይኖራቸዋል ።"

104 ባለው ሕግ "ዲተርሚኔሽን" የሚለው ቃል "አስረተይንሜንት" እንደሚለው ቃል ተደርጎ በስህተት ከፈረስንሳይኛ የተተረጐመው እንዲለውጥ ባለመደረጉ በረቂቁ ሕግ (የእንግሊዝኛ ቅጅ) መመሰቃቀሉ (ኮንፈውሽን) ብሷል ። በረቂቁ ሕግ ክፍል ፪ የተመለከቱት ሁኔታዎች (ከዚህ በታች ሀ ለ እና ሐ ይመልከቱ) አባትነት የሚመሠረትባቸው ሲሆኑ ፣ የአባትነት መኖር ግን የሚረጋገጠው የመወለድን ማስረጃ በሚመለከተው በረቂቁ ሕግ ክፍል ፬ ነው ።

105 በኢትዮጵያ ውስጥ የተለመዱ ናቸው ።

106 "አንቀጽ ፩፻፺. ማወቅ የሚፈጸምበት ሁኔታ (ፎርም):-አባትነትን ማወቅ በጽሑፍ ወይም በታወቀ ባሕላዊ ሁኔታ መደረግ አለበት ።"

107 "አንቀጽ ፪፻፷፯. በፍርድ ስለሚደረግ አባትነትን ማወቅ:-ልጁ ተረገዘ ተብሎ በሚገመትበት ጊዜ የልጁ እናት የድፍረት ሥራ ፣ ጠለፋ ወይም ማሳት የተፈጸመበት ከሆነ ፣ በዚሁ ወንጀል የተፈረደበት ሰው በፍርድ አባትነቱን እንዲያውቅ እንዲደረግ ክስ ሊቀርብበት ይችላል" (ሰረዝ የተጨመረ) ።

የመድፈር ሥራ በሚፈጸምበት ጊዜ አባትነት በፍ ርድ የሚታወቅ መሆኑን በመደንገግ ያለውን ሕግ (አንቀጽ ፯፻፶፫) ይዘት የሚያስተጋባ ከመሆኑም በላይ ፤ ይኸው "በማሳትም" ጊዜ ሊደረግ የሚ ችል መሆኑን ይገልጻል ። ሆኖም "ማሳት" የሚ መለከተው "እካለ መጠን ያልደረሱ" ሴቶችን ለመጠበቅ የተደነገገውን የወንጀለኛ መቅጫ ሕግ አንቀጽ ፭፻፺፮ በመተላለፍ ወንጀል መፈጸምን ("በፍርድ መቀጣት") መሆኑ በግልጽ ስለተጠ ቆመ ፤ በዚህ ሁኔታ አባትነት በፍርድ እንዲታወቅ ማድረግ በጣም ጠባብ ነው ። ይህ ከጋብቻ ውጭ እንደባልና ሚስት በመኖር በሕጋዊ ግምት አባት ነት የሚመሠረት በመሆኑ ይጠቀሙ የነበሩትን እካለ መጠን የደረሱ ሴቶችንም ጭምር አያጠቃ ልልም (በዚህ ሁኔታ ሕጋዊ ግምት በረቂቁ ሕግ ተሰርዞአል ፤ ከላይ ሁ-፫ ይመልከቱ) ።

በብዙ አገሮች ሕጎች በሕግ የልጁ መፀነሻ ተብሎ በሚ ገመተው ጊዜ ከጋብቻ ውጭ እንደባል ከእናትዮዋ ጋር አብሮ መኖር (በብዙ ሕብረተሰባዊ አገሮች እንደዚህ ነው) ወይም በማንኛውም ሁኔታ ከእናትዮዋ ጋር የግ ብረ ሥጋ ግንኙነት መፈጸም (ወንጀል ቢሆንም ባይ ሆንም) ፤ በፍርድ አባትነት እንዲታወቅ ክስ ለማቅረብ በቂ ነው ። ለእንዲህ ዓይነት ክሶች ምን መከላከያዎች ለማቅረብ እንደሚቻል ወይም እንደማይቻል ከአገር ወደ አገር ይለያያል ።[108]

## ለ - ፫ ላላ ያለ አመለካከት? ፪/ በመወለድ ማስረጃ

አሁን በሥራ ላይ እንዳለው ሕግ ሳይሆን "የመወለ ድን ማስረጃ" የሚመለከተው ረቂቅ ሕግ፤ "በጋብቻ የሚወለዱ ልጆችን" (ረቂቅ አንቀጽ ፪፻፸፯) እና "ከጋብቻ ውጭ የሚወለዱ ልጆችን" (ረቂቅ አን ቀጽ ፪፻፸፯) ለየብቻ ያያል ። ሆኖም የሁለቱም አን ቀጾች ንኡስ አንቀጽ (፩) ከዚህ በታች በ-ሐ በተጠ ቆሙት ምክንያቶች በሥራ ላይ ሊውል የማይችለ ውን የመወለድን ወይም የልደት ማረጋገጫ ጽሑ ፎችን በሚመለከት በመሠረቱ ተመሳሳይ ናቸው ። እንዲሁም "የሁኔታ መኖር"[109] በመወለድ ማስ ረጃነቱ ከነበረበት የሁለተኛ ደረጃ ወደሦስተኛ ደረጃ ዝቅ የሚያደርጉት የነዚሁ አንቀጾች ንኡስ አንቀጽ (፫) ተመሳሳዮች ናቸው ፡ ስለሆነም የሁ ለቱ ረቂቅ አንቀጾች መሠረታዊ ልዩነት የሚመ ነጨው ከንኡስ አንቀጽ (፪) አጻጻፉ ነው ።

ሀ/ የረቂቁ አንቀጽ ፪፻፸፯ (በጋብቻ የተወለዱ ልጆች) ንኡስ አንቀጽ (፪)[110] ክስ አቅራቢው የአባትነት ሕጋዊ ግምት እንዲኖር በሚያደርጉ ሁኔታዎች አባትነትን እንዲያረጋግጥ ይፈቅድለ ታል ። እነዚህ ሁኔታዎች በጋብቻው ጊዜ መወ ለድ ወይም መፀነስ ናቸው (ረቂቅ አንቀጽ ፪፻፶፩- ፩[111]) ። ሆኖም ሕግ አሻሻዩ "የሁኔታ መኖርን" (አንቀጽ ፯፻፺፱) ጨምሮ አሁን በሥራ ላይ ያሉ ትን የጋብቻ ማረጋገጫ ደንቦች (አንቀጽ ፯፻፳፪- ፯፻፳፯) ሰርዞአቸዋል ፡ ይህ ሁኔታ ፤ ብዙውን ጊዜ እንደሚሆነው ሁሉ የጋብቻ የምስክር ወረቀት ማቅረብ በማይቻልበት ጊዜ ፤ አባትነትን "በጋ ብቻ አማካይነት" ማረጋገጥን እንዳይቻል ያደ ርገዋል ።

ለ/ የረቂቁ አንቀጽ ፪፻፸፯ (ከጋብቻ ውጭ የተ ወለዱ ልጆች) ንኡስ አንቀጽ (፪)[112] ክስ አቅራ ቢው አባትነትን ለማረጋገጥ ማወቅ የተደረገበ ትን "ሰነድ" (ማወቁ በባህላዊ መንገድ በቃል ቢደረግስ ? ለ-፫-፩-ለ ይመልከቱ) ወይም በፍርድ አባትነት እንዲታወቅ የተደረገበትን ሰነድ (ሆኖም በፍርድ አባትነት የሚታወቅባቸው ሁኔታዎች ጠባብና የተለዩ ናቸው ፤ ለ-፫-፩-ሐ ይመልከቱ) እንዲያቀርብ ይፈቅድለታል ።

ከዚህ በላይ በተመለከቱት ችግሮች እንጻር ፤ በማስረጃነት ደረጃው በቲዎሪ ዝቅ የተደረገው "የሁኔታ መኖር" ፤ መወለድን በማረጋገጥ ረገድ በረቂቁ ሕግም ሰፊ ሚና መጫወቱን የሚቀጥል ይመስላል ።[113]

## ሐ/ የሕዝብ ክብር መዝገብ

አሁን በሥራ ላይ ያለውም ሆነ (አንቀጽ ፯፻፷፱) ረቂቁ ሕግ (ረቂቁ አንቀጽ ፪፻፸፯ እና ፪፻፸፯) መወ ለድ መረጋገጥ ያለበት በልደት ማረጋገጫ ጽሑፍ[114] መሆኑን በመሠረቱ ይደነግጉና ፤ ይኸው በሌለበት ጊዜ ግን መወለዱ በሌሎች ዘዴዎች እንዲረጋገጥ ይፈቅዳሉ ፤ በሌሎች አገሮች ብዙ ጊዜ የማያጋ ጥመው የልደት ማረጋገጫ ጽሑፍ አለመኖር በኢትዮጵያ አብዛኛውን ጊዜ የሚያጋጥም ስለሆነ ፤

---

108 በዚህ ረገድ ያሉትን ልዩነቶች ለመመልከት የተለየ ጽሑፍ ማዘጋጀት ያስፈልጋል ። ለምሳሌ የፖላንድን የቤተሰብ ሕግ አንቀጽ 85-86 ይመልከቱ ። እንዲሁም የአንዳንድ ምዕራባውያን አገሮችን አመለካከት የሚጠቀመውን (ስለሶቭየት ሕግ የተጻፈው አሁን የሚሠራበትን የሚመለከት ስላልሆነ ማለፉ ይሻላል) በዲ. ላዛክ ፤ ፖሊሽ ፋሚሊ ሎው (ሎይደን ፲፱፻፷፰ ከገጽ 162-165) ይመልከቱ ። አዲስ የሕግ መሻሻሎች ከጋብቻ ውጭ ለተወለደ ልጅና ለእናቱ ያደላሉ ፤ ለምሳሌ ፤ ፒ ሲዱዊን ፤ ሶቭየት ሌጅስሌሽን ኦን ማሬጅ ኤንድ ፋሚሊ (ሞስኮ ፤ ፲፱፻፸፫) ይመልከቱ ።

109 ለ "ሁኔታ መኖር" በረቂቁ አንቀጽ ፪፻፸፯ የተሰጠው ትርጉም አሁን በሥራ ላይ ባለው ሕግ አንቀጽ ፯፻፰ (፩) ከተሰጠው ትርጉም ጋር አንድ ነው ።

110 "የመወለዱን የምስክር ወረቀት ለማቅረብ የማይቻል ከሆነ መወለዱ የአባትነት ሕጋዊ ግምት እንዲኖር በሚያደርጉት ሁኔታዎች ሊረጋገጥ ይቻ ላል ።" ይላል ።

111 "በጋብቻው ጊዜ የተፀነሰ ወይም የተወለደ ልጅ አባቱ ያው የእናትዮዋ ባል ነው ።" ይላል ። ይህ አሁን በሥራ ላይ ካለው ሕግ አንቀጽ ፯፻፵፰ አጻ ጻፍ ጋር አንድ ነው ።

112 የልደቱን ማረጋገጫ ጽሑፍ ለማቅረብ የማይቻል ከሆነ ፤ መወለዱ ፤ ማወቁ የተደረገበትን ሰነድ ወይም አባትነትን ማወቁ በፍርድ እንዲደረግ የታ ዘዘበትን የፍርድ ቤት ሰነድ በማቅረብ ሊረጋገጥ ይችላል ።" ይላል ።

ይህ የሚሆነው "....................ሰነዶችን ሳለማቅረብ በቂ ምክንያት ካለ መወለድ በሁኔታ መኖር ሊረጋገጥ ይችላል" (ረቂቁ አንቀጽ ፪፻፸፯-፫) የሚለውን ፍርድ ቤቶች በጠባቡ ካልተረጎሙት ነው ። ሰነዶቹ መጀመሪያውኑ ባይኖሩስ ?

114 በተምቀት ማረጋገጫ አይደለም ።

መወለድን በሌሎች ይኸን ያህልም አስተማማኝ ባልሆኑ ዘዴዎች (በተለይም "በሁኔታ መኖር") ማረጋገጥ የግድ አስፈላጊ ነው ። መወለድን በልደት ማረጋገጫ ጽሑፍ ማረጋገጥ የሞት ፣ የጋብቻና የመወለድ ሁኔታዎች በሚመዘገቡበት በሕዝብ ክብር መዝገብ ችግሮች መፍትሔ ማግኘት ላይ ይመሰረታል ።

የሕዝብ ክብር መዝገብን የሚመለከቱ ደንቦች አብዛኛውን ጊዜ የፍትሐ ብሔር ሕግ አካል አይደሉም ። የሕዝብ ደህንነትን (ጥቅምን) የሚመለከቱ ስለሆነ የአስተዳደር ሕግ አካል ናቸው ። አስተማማኝ የሆነ የመወለድ ፤ የጋብቻና የሞት ዝርዝር ሁኔታዎችን የሚያብራራ መዝገብ መኖር አንድ ዘመናዊ ሕብረተሰብ የአስተዳደር ፣ የማህበራዊ ፣ የኤኮኖሚና የወታደራዊ ዕቅዶቹን በትክክል እንዲነድፍ ያስችለዋል ። ሆኖም ይህ በዚህ ሁኔታ ተመዝግበው የተያዙ ጽሑፎች በፍትሐ ብሔር ሕግ ላይ የሚኖራቸውን ጠቃሚ ሚና አያስቀረውም ። ምክንያቱም ውጤታቸው በአንድ ሰው መወለድ ፤ ጋብቻ ወይም ሞት ለሚወሰኑ የፍትሐ ብሔር ጉዳዮች እነዚህ ጽሑፎች በቅድሚያ የተዘጋጁ አስተማማኝ ማስረጃዎች ስለሚሆኑ ነው ። እ ኤ አ በ፲፱፻፵፩ ዓ/ም በወጣው "የማዘጋጃ ቤቶች አዋጅ" መጠነኛ ሙከራ ተደርጎ የነበረ ቢሆንም ፣[115] በ፲፱፻፶፪ ዓ/ም የፍትሐ ብሔር ሕጉ በታወጀበት ጊዜ አጠቃላይ የሆነ የሕዝብ ክብር መዝገብ አሠራር ለመፍጠር ተጨባጭ ሁኔታዎች የተሟሉ አልነበሩም ። ይሁን እንጂ የፍትሐ ብሔር ሕጉ (አንቀጽ/ታይትል/፭ ምዕራፍ ፫) የክብር መዝገብ ጽሑፎቹንና የክብር መዝገብ ሹሞችን የሚመለከቱ የተብራሩ ደንቦችን የያዘ ሲሆን ፤ እነዚህ ደንቦች ግን በመሸጋገሪያ አንቀጽ ፫ሺ፫፻፷፩-፭ አማካይነት "በነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ትእዛዝ እስከሚወጣበት ቀን ድረስ" በሥራ ላይ እንዳይውሉ ታግደዋል ። በሥራ ላይ እንዲውሉ እስካሁን ያልተደረገ ሲሆን ወደፊትም በቅርቡ የሚቻል አይመስልም ። ሆኖም በቅርቡ በወጣው "የከተማ ኗሪዎች ማህበራትና የማዘጋጃ ቤቶች አዋጅ ቁጥር ፩፻፬/፲፱፻፸፮" አማካይነት በተፈጠሩት ፍሬአማ እድገቶች አኳያ ለወደፊቱ ተስፋ ሊደረግ ይችላል ። በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፱/፲፬ መሠረት "ከቀበሌ ኗሪዎች ማህበራት ግዴታዎች አንዱ" በቀበሌው ውስጥ የሚሆኑትን መወለዶች ፣ ጋብቻዎችና ሞቶች የሚመለከት መዝገብ መያዝ ነው ። በዚህ ሐረግ የተጠቀመው ዓላማ በሥራ ላይ እንዲውል ግን ከዚህ በታች ከተመለከቱት አቅጣጫዎች ባንዱ ተጨማሪ የአፈጻጸም ደንቦችን ማውጣት ያስፈልጋል ፤ ይኸውም ፤

— ወረዳ በወረዳና ቀስ በቀስ የታገደውን የፍትሐ ብሔር ሕግ አንቀጽ /ታይትል/፭ ምዕራፍ ፫ አንዳንድ አንቀጾች በሥራ ላይ እንዲውሉ በማድረግ ፤ ወይም

— የታገደውን የፍትሐ ብሔር ሕግ ክፍል በሌላ ተስማሚ ክፍል በመተካት ከላይ እንደተጠቀመው ቀስ በቀስ በሥራ ላይ እንዲውል በማድረግ[116] ሊሆን ይችላል ።

የሕዝብ ክብር መዝገብን የሚመለከተው ክፍል አለመሟላት ከሚያስከትላቸው ውጤቶች ፣ በተለይም የሚከተሉት በመወለድ ሕግ ተመራማሪዎች ትኩረት ሊደረግባቸው ይገባል ።

ቀደም ሲል እንደተጠቀመው ብቸኛና ትክክለኛ የሆነው የማያከራክር የእናትነት (የሪፖርቱን ሁ-፪ ይመልከቱ) እና የአባትነት (የሪፖርቱን ሉ-፪) ማረጋገጫ ዘዴ (የሪፖርቱን የግርጌ ማስታወሻ ቁጥር ፯ ይመልከቱ) የሁኔታ መኖር ነው ። በዚህ ደረጃ በአንቀጽ ፯፻፷፱ (እና አንቀጽ ፯፻፹-፭) ላይ "የልደት ማረጋገጫ ጽሑፍ" የሚለው ሐረግ በታገደው የፍትሐ ብሔር ሕግ አንቀጽ (ታይትል) ፭ ምዕራፍ ፫[117] የተመለከተውን ጽሑፍ እንጂ ሌላ ለማለት አለመሆኑን ማብራራት ያስፈልጋል ። "የልደት ማረጋገጫ ጽሑፍ" የሚለው ሐረግ ከአጠቃላይ ሁኔታዎች ጋር መታየት አለበት ። በ"ሕግ" መሠረት በተዘጋጀ "ጽሑፍ" የጋብቻን መረጋገጥ የሚደነግገው አንቀጽ ፮፻፺፰ ፣ ለዚሁ አንቀጽ አፈጻጸም "ሕግ" ማለት የሕዝብ ክብር መዝገብን እና ሹሞችን የሚመለከተው የታገደው የምዕራፍ ፫ አንቀጾች መሆናቸውን ከሚጠቁሙት ከአንቀጽ ፯፻፷(፫) እና ፯፻፺ (፫) ጋር አብሮ እንደሚነበበው ሁሉ ፤ መወለድ በልደት ማረጋገጫ ጽሑፍ መረጋገጥ ያለበት መሆኑን የሚደነግገው አንቀጽ ፯፻፷፱ እንደዚሁ ፤ የተባለው ጽሑፍ የታገዱት አንቀጾች ከታወጁ በኋላ በእነዚሁ መሠረት የተዘጋጀ መሆኑን ከሚጠቁሙት ከሌሎች የቤተሰብ ሕግ አንቀጾች ጋር አብሮ መታየት ይኖርበታል ። በእርግጥም "የልደት ማረጋገጫ ጽሑፍ" በመጀመሪያ ደረጃ የሚገኝ የመወለድ ማረጋገጫ መሆኑ ትርጉም የሚኖረው ፤ ለዚሁ ሰነድ ከፍተኛ የአስረጅነት ድርሻ[118] የሚሰጠው የታገደው አንቀጽ ፶፯ (ወይም ሌላ ተመሳሳይ አንቀጽ) ከሌሎች የሕዝብን ክብር መዝገብ ትክክለኛነት ከሚያረጋ

115 አዋጅ ቁጥር 74 ፤ አንቀጽ ፱ ። የማዘጋጃ ቤት ባለሥልጣን ጋብቻ በሚያስፈጽምበት ጊዜ እንኳን የጋብቻውን ውል በመዝገብ አይመዘግብም ።

116 የሕግ አሻሻዩ ኮሚቴ የታገደውን ክፍል የሰረዘው ሲሆን በምትኩም ሌላ አላስገባም (ጉዳዩን ለአስተዳደር ሕግ በመተው ይሆን ?)

117 አንቀጽ ፫ሺ፫፻፷፭(፩) ለምንነጋገርበት ርዕስ አግባብ የሌላቸውን አንቀጾች ፶፯ ፣ ፰፭ ፣ ፹፰ እና ፫፻፴፪ አያግድም ።

118 በአንቀጽ ፶፯ መሠረት ደንበኛ ሆነው የተመዘገቡ የክብር መዝገብ ጽሑፎችን ለመቃወም ማስረጃ ለማቅረብ "የዳኞች ፈቃድ ያስፈልጋል" ። ስለ ሆነም በእርግጥ አባት ሳይሆን በእናትየዋ አባት መሆኑ ተጠቅሶ ይኸው በደንበኛ በክብር መዝገብ የተመዘገበበት ሰው ይኸው የምዝገባ ስህተት እንዲታረምለት ለመጠየቅ በመጀመሪያ የፍርድ ቤት ትእዛዝ ማግኘት አለበት (አንቀጽ ፩፻፷፭) ።

ግጡ የታገዱ አንቀጾች ጋር አብሮ መታወጁን መገንዘብ ሲቻል ብቻ ነው ። እነዚህም የሚገኙት ፤

— በአንቀጽ ፸፱-፹፱ (የሕዝብ ክርብ መዝገቦችን ይመለከታል) ፤

— በአንቀጽ ፺-፺፰ (በመዝገቦቹ የሚመዘገቡትን ጉዳዮች ይመለከታል) ፤

— በአንቀጽ ፺፱-፩፻፫ (በተለይም የልደትን ማረጋገጫ ጽሑፍ ይመለከታል) ፤ እና

— በአንቀጽ ፩፻፴፰-፩፻፵፮ (በሕግ መሠረት አለመፈጸም የሚያስከትላቸውን ቅጣቶች ይመለከታል) ነው ።

በተለይም ከዚህ የሚከተሉትን በጥሞና መመልከት ይገባል ፤

ሀ/ የልደት ማረጋገጫ ጽሑፍ ሕጻኑ በተወለደ በሦስት ወራት ውስጥ በሕዝብ ክብር መዝገብ መመዝገብ አለበት (አንቀጽ ፹፱-ሀ) ። ይህ የሆነው ሁኔታውን የሚገልጹት ሰዎች በሕይወት እያሉና ነገሩን "ሳይዘነጉት" ምዝገባው የሚደረግ መሆኑን ለማረጋገጥ ነው ። ጽሑፉ በክብር መዝገብ ካልተመዘገበ ወይም በክብር መዝገብ እንዲገባ የተደረገው የተጠቀሰው የጊዜ ገደብ ካለፈ በኋላ ከሆነ (በፍርድ መሠረት ካልሆነ በስተቀር) በመዝገቡ ውስጥ እንደተጻፉ ጽሑፎች ሳይሆን እንደተራ ማስረጃ ብቻ ይቆጠራል (አንቀጽ ፺፰ እና ፹፫) ።

ለ/ የልደት ማረጋገጫ ጽሑፍ አባት እና እናትን መግለጽ አለበት (አንቀጽ ፺፱-መ) ።

ሐ/ ሕፃኑ ሲወለድ ይኸው በአባቱ ፣ ወይም እሱ ይህን በማያደርግበት ጊዜ በእናቱ (ወይም በአሳዳጊው ወይም በጠባቂው) አለዚያም መወለዱን የሚያውቅ ከሆነ በሕዝብ ክብር መዝገብ ሹሙ መገለጽ አለበት (አንቀጽ ፩፻፩) ። በሌሎች አገሮች እንደሚደረገው ሁሉ[119] ይህ ግዴታ በሌሎች የልጁን መወለድ ባዩ ሰዎች ላይም ቢኖር ጥሩ ነው ።

መ/ መወለዱን የመግለጽ ግዴታ ያለባቸው ሰዎች በተጠቀሰው የሦስት ወር ጊዜ ውስጥ መወለዱን ሳይገልጹ ቢቀሩ ፣ ወይም ለመግለጽ እምቢተኛ ቢሆኑ ፣ ወይም እያወቁ የተሳሳተ መግለጫ ቢሰጡ በሕግ ይቀጣሉ (አንቀጽ ፩፻፴፱-፩፻፵፫) ።

የእነዚህ ዓይነት አንቀጾች አለመኖር የሕዝብ ክብር መዝገብ ለመንግሥት ስታቲስቲክስ የሚያበረክተውን ዋጋ ላይነካው (ላይጎዳው) ይችላል ። ሆኖም መወለድን ማረጋገጥን ጨምሮ ፍትሐ ብሔር ሕግን በሚመለከት የሚያበረክቱትን የማስረጃነት ዋጋ በጣም ይቀንሰዋል (ይጎዳዋል) ። እንዲያውም ትክክለኛ ለመሆናቸው መጠባበቂያ ካልተደረገላቸው ከሕዝብ ክብር መዝገቦች የሚገኝ ሐሳብ በረቂቁ ሕግ አንቀጽ ፯፻፶፯-፯፻፷፯ የሁለተኛ ደረጃ ከተሰጣቸው ሰነዶች ከሚገኝ ሐሳብ ያነሰ ሊሆን ይችላል ።

## በመጨረሻ የታከለ

በዚህ ሪፖርትም ሆነ በተጨማሪው መወለድን በ[illegible] መለከት ረገድ መሠረታዊ የሆኑ አማራጭ የፖሊሲ ሐሳቦች አላቀረብሁም ። ይሁን እንጂ በዚህ የመጨረሻ ማከያ ላይ የኢትዮጵያ የመወለድ ሕግ በጣም ላላ ባለ አኳኋን መሻሻል ያለበት ስለመሆኑ (የማከያውን ሉ-፫ ይመልከቱ) ያለኝን አስተያየት በአጭሩ ብጠቁም እንደ ስህተት የሚቆጠር አይመስለኝም መሻሻል ያለበት መሆኑን የሚደግፉ ምክንያቶች የሚከተሉት ናቸው ።

፩/ ይህ ፖሊሲ በብዙ ሶሻሊስትና አንዳንድ ሶሻሊስት ባልሆኑ አገሮች[120] ግልጽ በሆኑ ሰብአዊ እና/ ወይም የእኩልነት ምክንያቶች በሥራ ላይ ውሏል ።

፪/ በተለይም ይህ ፖሊሲ ብዙ አባት የለሽ ልጆች ባሉበትና እነዚህንም በድጋፍ ለማሳደግ (ሶሻል ዌልፌር) መንግሥት ሕግ ለማውጣት በማይችልበት በኢትዮጵያ ሁኔታ ተቀባይነት ሊኖረው ይገባል ።

፫/ አካለ መጠን ያልደረሰን ልጅ በልማዳዊ ሁኔታ ማሳደግ የሚያስከትለው ወጭ በኢትዮጵያ በጣም ቀላል ስለሆነ ፣ ከጋብቻ ውጭ የወለደ አባት ይኸንን ወጭ በቀላሉ ሊሸፍነው ይችላል ።

ስለዚህ የሚከተሉት እርምጃዎች እንዲወሰዱ ሐሳብ አቀርባለሁ ።

፩/ በአንቀጽ ፯፻፵፰ የተደነገገው የአባትነት ሕጋዊ ግምት በአንቀጽ ፯፻፵፫ በተመለከተው ከጋብቻ ውጭ እንደባልና ሚስት አብሮ መኖርንም በሚመለከተው ረገድ ተፈጻሚነቱ እንደተጠበቀ እንዲቆይ ፤

፪/ ከአንቀጽ ፯፻፵፰-፯፻፶፩ ያለውን በመሰረዝ በምትኩ ልጁ ከተወለደበት ጊዜ በፊት ከ፫፻ እስከ ፩፻፹ ቀኖች ባለው ጊዜ ውስጥ ከእናትዮዋ ጋር የግብረ ሥጋ ግንኙነት በፈጸመ ሰው ላይ በፍርድ አባትነቱን እንዲያውቅ ክስ ለማቅረብ የሚያስችሉ አንቀጾች ማስገባት ። በዚህ ሁኔታ ለሚቀርብ ክስ የሚከተሉት እንደመከላከያ ሊወሰዱ ይችላሉ ።

ሀ/ በተባለው ጊዜ ውስጥ እናትዮዋ ግልጽ በሆነ ሁኔታ በሽርሙጥና በመሰማራት የቆየች ከሆነ ፤ ወይም

119 ለምሳሌ የፈረንሳይ ፍትሐ ብሔር ሕግን አንቀጽ ፶፮ ይመልከቱ ።

120 በግርጌ ማስታወሻ ቁጥር 118 የተጠቀሰውን ይመልከቱ ። እንዲሁም ጅ. ጋሪሲያ ካንቴሮ ፣ "ለ ሲቲዊስን ጁሪዲክ ዴዝ ኢንፋንት ኔስ ሆርስ ማሪጅ" በ ራፖርትስ ዲኔሩ አ ኮንግሬስ ኢንተርናሲዮናል ዱ ድርዋት ኮምፓሬ (ብራስልስ ፣ ፲፱፻፷፪) ውስጥ የተጻፈውን ለምሳሌ ገጽ 348 ይመልከቱ ።

ለ/ ተከሳሹ ለመውለድ የማይችል መሆኑ[121] ወይም በደም ምርመራ የልጁ አባት አለመሆኑ ከተረጋገጠ ፤
ወይም

ሐ/ በተባለው ጊዜ ውስጥ እናትየዋ ከሌላ ሰው ጋር የግብረ ሥጋ ግንኙነት የፈጸመች ከሆነና የዚሁ ሰው አባት መሆን የበለጠ አስተማማኝ[123] ከሆነ ። ለዚህ መመዘኛዎች ሰውየው ከሴትዮዋ ጋር ግንኙነት ያደረገበት ጊዜ ብዛት ፣ ወይም/እና ግንኙነቱ የተደረገበት ጊዜ (አማካይ መሆኑ) ፣ ከልጁ ጋር ያለው መመሳሰል ፣ የባለሙያ (ጀይኖኮጅስት) አስተያየት ወዘተ ሊሆኑ ይችላሉ ።

መ/ በመጨረሻ ይርጋ[124] ።

በመጨረሻም ፣ የሕግ አሻሻዩ ኮሚሽን አባሎች በሙሉ ወንዶች ስለሆኑ ፣ ከዚህ በላይ የተጠቀሙትን ነጥቦች በሚመለከት ረገድ የኢትዮጵያን የሴቶች ማህበር ማማከሩ ጠቃሚ ሊሆን እንደሚቻል መጠቆም እወዳለሁ ።

121 ለጽንስ መከላከያ የሆኑ መድኃኒቶች ይወሰዱ የነበረ መሆኑን መጨመሩ በማስረጃ ረገድ ከፍተኛ ችግሮች ያስከትላል ።

122 ኤክሴፕቲኦ ፕሎሪየም ኮንኩምቤንቲየም ተብሎ የሚታወቀው መከላከያ ነው ።

123 የፖላንድ የቤተሰብ ሕግ አንቀጽ ፹፭(፪) የሚደነግገው (ይህ በ፲፱፻፸፭ ዓ/ም በተደረገው የሕግ መሻሻል አልተለወጠም) ። እንዲሁም ለዞክን ከገጽ 164-165 ይመልከቱ (በግርጌ ማስታወሻ ቁጥር 108 ተጠቅሶአል) ።

124 በአንዳንድ አገሮች ልጁ የሚያቀርበው ክስ (ብዙ ጊዜ በእናትየዋ የሚቀርብ) ጥብቅ የይርጋ ገደብ አለበት ። በጣም አጭር በሆነበት በአውስትሪያ አንድ ዓመት ነው ። (ሲቪል ጀስትዝቡች ፣ አንቀጽ ፪፻፷፫) ። ከላይ የተጠቀሰውን ለዞክን የግርጌ ማስታወሻ ቁጥር 108 ገጽ 161 ቁጥር 130 ይመልከቱ ። ዓላማው የማይረቡ ክሶችን በማምጣት የሚፈጸመውን ለመቆጣጠር ይመስላል ። ይህ የይርጋ ገደብ በሕጋዊ ግምት ወይም በማወቅ ወይም በልደት ማረጋገጫ ጽሑፎች ወይም በሁኔታ መኖር የሚመሠረቱ መወለዶችን አይመለከትም ።